ማውጫ

ርዕስ ገጽ

መግቢያ 1

ምዕራፍ አንድ 1

1. ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን . . . . . .

1.1 የሕንፃ ቤተክርስቲያን አሰራርና አገልግሎት 3

1.2 የሦስቱ ክፍሎች አገልግሎትና ምሳሌዎች 4

1.3 የቤተክርስቲያን አሰራር ምሳሌዎች 6

1.4 ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊያውቁአቸው ፣ ሊያደርጉአቸውና
ሊጠብቁአቸው የሚገቡ ስርዓቶች 7

1.5 ሥርዓተ ፀሎት 9

1.6 ሥርዓተ አቲብ/የማማተብ ሥርዓት /. 12

ማጠቃለያ 13

ምዕራፍ ሁለት 14

2. ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን 14

2.1 ምሥጢረ ጥምቀት 15

2.2 ምሥጢረ ሜሮን 18

2.3 ምሥጢረ ቁርባን 21

2.4 ምሥጢረ ክህነት 23

2.5 ምሥጢረ ተክሊል 26

2.6 ምስጢረ ንሰሐ 29

2.7 ምሥጢረ ቀንዲል 34

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

መግቢያ

‹..... በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው::› 1ኛ ጢሞ 3፥15

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በወንጌል ለወለደው ልጁ ጢሞቴዎስ ብዙ ነገሮችን መክሮታል አስተምሮታል:: /1ኛ ጢሞ 3፥1-13፤ 5፥1-25/ ከእነዚህም መካከል በቤተክርስቲያን ለአገልግሎት ሲመላለስ በሥርዓት መሆን እንዳለበትም ያስተማረው ተጠቃሽ ነው::

የፍጥረታት ባለቤት አምላካችን እግዚአብሔር እንኳን አእምሮ ለሰጠው ለሰው ልጅ ይቅርና ለግዑዛኑ ፍጥረታትና ለእንስሳትም ሳይቀር የኑሮ ሂደታቸውን በሥርዓት እንዲመሩ አድርጐ ነው የፈጠራቸው::

በመነሻችን ላይ የተጠቀሰው ቃል በዘመናችን በቤቱ ለጸሎት፣ ለስግደት፣ለአገልግሎት ... ለምንመላለስ ክርስቲያኖች ማድረግ ያለብንና የሌለብንን ለይቶን ማወቅ እንዳለብን ያስገነዝበናል::

የዚህ ትምህርትም ዓላማው ማንኛውም በእግዚአብሔር ቤት ሲመላለስ ምን ማድረግ እንዳለበትና እንዲሁም ስለ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ሁኔታ ለማሳወቅ ይረዳ ዘንድ ነው:: በውስጡም የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አሠራር፣ የመቅደስ፣ የጸሎት፣የማኅሌት፣ሥርዓቶችን ተካተዋል::

የቤተ ክርስቲያን ጉልላትና ራስ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢሩን ይግለጽልን:: አሜን::

ምዕራፍ አንድ

1. ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን

የቃሉ ትርጉም -- ሥርዓት ማለት፣ ሠርዓ ክሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ደንብ መሠረተ፣አደረገ ማለት ነው።

ቤተክርስቲያን ማለት -- በግዕዝ ቤተ የሚለው ቤት ማለት ሲሆን ትርጉሙ ማደሪያ ማለት ነው። ክርስቲያን ማለት ደግሞ የክርስቶስ ተከታይ ማለት ነው። በጥምረት ሲፈታ የክርስቶስ ማደሪያ፣የክርስቲያኖች ቤት ማለት ነው። ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ማለት ደግሞ ምዕመናን ለእግዚአብሔር መገዛታቸውን የሚገልጹበት የአምልኮ መመሪያ፣ ደንብ ማለት ነው። ይኸውም የጸም፣የጸሎት፣የስግደት፣የመቅደስ ወዘተ.... ሥርዓቶች ናቸው።

የቤተክርስቲያን ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በዘይቤም በምስጢርም ሦስት/3/ ዓይነት ትርጉም ይዞ እናገኘዋለን እነርሱም

1. ሕንፃ ቤተክርስቲያን
2. ማኅበረ ምዕመናን
3. የአንድ ክርስቲያን ሰውነት ናቸው።

1. **ሕንፃ ቤተክርስቲያን** - ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ በትንቢቱ ‹...ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ። በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ....› ይላል። /ኢሳ 56፥7/ ይህን የተቀደሰ ተራራ አምላክ ኤልያስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ወደ መቅደሱ ገብቶ በጅራፍ እየገረፈ ገብያተኛውን ካስወጣ በኋላ ‹ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላል...› ሲል ያስከበረው ቤተክርስቲያንን ነው። /ማቴ 21፥12-13/

አንድን ሕንፃ ቤተክርስቲያን፣ ቤተክርስቲያን የሚያሰኘው

1. የቃል ኪዳኑ ታቦት በውስጡ ስለሚገኝበት /2ኛ ዜና 5፥2-10/

2. በቅዱስ ሜሮን ስለከበረ /1ኛ ዮሐ 2፥20/
3. አማናዊው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ስለሚፈተትበት /ዮሐን 6፥33-53/ ነው።

በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን የጸሎት፣የትምህርት፣የድኅነት፣የቃል ኪዳን፣ የበረከት፣የሠላም ወዘተ... ቤት ናት። /ማር 11፥17/

2. **ማኅበረ ምዕመናን** - የክርስቲያኖች ስብስብ/ኅብረት/ ማለት ነው። ይኸውም የነቢያትና የሐዋርያት እምነት፣ሥርዓትና ትውፊት የተቀበሉትን /የያዙትን/ ነው። ኤፌ 2፥20 የተጀመረውም በማርቆስ እናት ቤት ነው። ሐዋ.11፥26
3. **የአንድ ክርስቲያን ሰውነት** - በ40 እና በ80 ቀኑ የተጠመቀ ከአሕዛብነት ተመልሶ/አምኖ/ ተጠምቆ ሃብተ ወልድና ስመ ክርስትና አግኝቶ በእምነት በምግባር የፀና /በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት የጸና እምነት ያለው ቤተመቅደስ /ቤተክርስቲያን/ ይባላል። 1ኛቆሮ 3፥16 2ኛ.ቆሮ 6፥16

1.1 የሕንፃ ቤተክርስቲያን አሠራርና አገልግሎት

በሀገራችን የተለያዩ የቤተክርስቲያን አሠራር ያለ ቢሆንም በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/ግን ሦስት አይነት አሠራር አለ።

1. ክብ ቅርፅ 2.. ሰቀላማ ቅርፅና 3. ዋሻ ቅርፅ ናቸው።

1. **ክብ ቅርፅ ቤተክርስቲያን** - በሀገራችን ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ የሚገኘው የቤተክርስቲያን አሠራር ይኸኛው ስልት ነው። በዚህ አሠራር አጥር ቅጥሩም ክብ ሲሆን አሠራሩም በሁለት ይከፈላል።

ሀ. <u>ቤተ ንጉሥ/ሙሉ ክብ/</u> - በዚህ አሠራር የቅኔ ማኅሌት፣ቅድስትና መቅደሱን የሚለዩበትም ግድግዳዎች ክብ ይሆናሉ ወይም መቅደሱ 4/አራት/ ማዕዘን ሆኖ ከምህዋር በላይ ክብነቱን የጠበቀ ይሆናል። ክዳኑም በሣርም በቆርቆሮም ሊሠራ ይችላል። ጉልላቱም አንድ ነው።

ለ. <u>ባለ ጎን ክብ ማለትም</u> - ባለ 8፣10፣12 ወዘተ... ጎን/ማዕዘን/ ያለው የቤተክርስቲያን አሠራር ነው። በፈረንጆቹ /Hexagon, Octagon/ ይባላል። ማለትም ሙሉ ክብ ያልሆነ ለምሳሌ ቅዱስ ሩፋኤል፣ቅድስት ልደታ፣ቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ወዘተ... ከባለ ጎን ክብ ቤተክርስቲያን የሚመደቡ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜም የዚህ ዓይነት አሠራር ክዳኑ ሁለት ደረጃ አለው።

የክብ ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ በር መጋረጃ አለው። በዚህ ክፍል አናት ላይ መሶበ ወርቅ የሚመስልና መስቀል ይደረጋል። በመስቀሉ ላይ ምሳሌነት ባለው ቁጥር 3፣5፣6፣7፣12 የሰጎን እንቁላል ይሰካበታል። ይኸውም የተዘክሮተ እግዚአብሔር ምልክት ነው። በክብ ቤተክርስቲያን 3 በር መኖሩ የሥላሴ ምሳሌ ነው።

2. **ሰቀላማ ቤተክርስቲያን** - የዚህ ዓይነት የቤተክርስቲያን አሠራር የተወረሰው ከሰሎሞን ቤተመቅደስና በዘመነ ክርስትና ታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናቱ ቅድስት ኢሌኒ በኢየሩሳሌምና በቤተልሔም ካሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ነው። ለምሳሌ ደብረዳሞ፣ አክሱም ወዘተ.... በዚህ ዓይነት የቤተክርስቲያን አሠራር መነሻነት በዘመናችን ዘመናዊ የሆኑ አሠራሮች አሉ ምድባቸው ሰቀላማ ሆኖ በቅርጽ ለየት ያሉ ናቸው። ለምሳሌ ሞላላ ቅርፅ ያለው አሠራር አለ ለአብነት የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተክርስቲያን መጥቀስ ይቻላል ።

- ቅኔ ማኅሌቱ፣ ቅድስቱና መቅደሱ የሚለዩት በደረጃ ነው። በሩም የተወሰነ አይደለም 4ትም 5ትም ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል። ወንዶችና ሴቶች ግራና ቀኝ ሆነው ያስቀዱሱበታል።

3. **ዋሻ ቅርጽ የቤተክርስቲያን** - ይህ ዓይነት አሠሪር የቅዱሳን የተጋድሎ ውጤት የሚነበብባቸው አስቸጋሪ የሆነውን የቋጥኝ አካል በመፈልፈል የገነቧቸው ተራራን ተገን በማድረግ የሚሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። በራቸው አንድ ሲሆን ጉልላት የላቸውም 3ቱም ክፍሎች የሚለዩት በመጋረጃ ነው። ከአንድ ቋጥኝ የሚፈለፈሉ ከተራራ ተገኖመው የሚሠሩ ፍልፍል ቤተ መቅደሶችም ከዚህ ጋር ይመደባሉ። ለምሳሌ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን መጥቀስ ይቻላል።

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው የቤተ ክርስቲያን አሠራር ይለያይ እንጂ አገልግሎቱ አንድ ነው። በምንም ይሠራ አንዱ ከንዱ አይበልጥም አያንስምም ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናትና።

1. 2 የሦስቱ ክፍሎች አገልግሎትና ምሳሌዎች

ቤተክርስቲያን በክብም ሆነ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አሠራሮች ቢሰራ 3 ክፍል ሊኖረው ይገባል። እነዚህም ቅኔ ማኅሌት፣ቅድስት እና መቅደስ ናቸው። የእነዚህ ክፍሎች ጠቀሜታ ጎልቶ የሚታወቀው በክብ የቤተ ክርስቲያን አሠራር ነው። የመጀመሪያው ክፍል።

1. **ቅኔ ማኅሌት** - ስያሜው ከግብሩ የተወሰደ ሲሆን መዘምራን ካህናት ስብሐት እግዚአብሔር ያደርሱበታል። በምሥራቅ በሰሜንና በደቡብ ሦስት በሮች ሲኖሩት

በእነዚህም በሮች ካህናት፣ወንዶችና ሴቶች ሲገቡበት የወንዶችና የሴቶች መቆሚያው ደግሞ በመጋረጃ ይለያያል። ዘጸ 25፥8 ፤ ዘጸ 26፥33-34


2. **ቅድስት** - ቀጥተኛ ትርጉሙ የተለየ ልዩ ማለት ሲሆን በተለይም ለክብ ቤተክርስቲያን ማዕከላዊ ነው።

- ይህ ክፍል ካህናት በድርገት ጊዜ ምእመናንን የሚያቆርቡበት ክፍል ነው። በምዕራብ በኩል ቆሞሳት፣ቀሳውስት እና ዲያቆናት ፣በሰሜን በኩል ደናግል፣የቀሳውስትና የዲያቆናት ሚስቶች ቆመው ያስቀድሱበታል። ሥርዓተ ተክሊል ይፈጸምበታል። በምዕራብ፣በምሥራቅ፣በሰሜንና በደቡብ አራት በሮች አሉት።

3. **መቅደስ** - በብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን በሚል ስያሜ ከሚታወቀው ውስጠኛው ክፍል ጋር የሚነጻጸር ሲሆን በአሁኑ ወቅት የቃልኪዳኑ ታቦት ይገኝበታል። በዚህ ክፍል ብፁዕወቅዱስ ፖትርያርኩ፣ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያስቀድሱበታል።

- በምዕራብ፣በሰሜንና በደቡብ ሦስት በሮች ሲኖሩት እያንዳንዱ በር መንጦላዕት/መጋረጃ/ አለው።
- ሦስቱ ክፍሎች የሦስቱ ዓለመ መላእክት ማለትም
    - ቅኔ ማኅሌት - የኤረር
    - ቅድስት - የራማ
    - መቅደስ - የኢዮር ምሳሌ ናቸው።
- የሦስቱ ማዕረገ ክህነት፣ የዲቁና፣የቅስና፣የጵጵስና ምሳሌ ነው።
- የሦስቱ ጾታ፣ ምዕመናን የካህናት፣የወንዶች እና የሴቶች ምሳሌ ነው፡

የመቅደስ፣ ቅድስትና ቅኔ ማኅሌት ስዕላዊ መግለጫ



አቅጣጫዎች

- መስዕ - በሰሜንና በምሥራቅ መካከል የሚገኝ አቅጣጫ
- ሌባ - በምሥራቅና በደቡብ መካከል የሚገኝ አቅጣጫ
- አዜብ - በምዕራብና በደቡብ መካከል የሚገኝ አቅጣጫ
- ባሕር - በምዕራብና በሰሜን መካከል የሚገኝ አቅጣጫ

1›3 የቤተክርስቲያን አሠራር ምላሌዎች

- የቤተክርስቲያን ራሷ የኢየሩሳሌም ሰማያዊት ምሳሌ ናት። ዕብ 9
- መሠረቷ የቅዱስ ጴጥሮስ ምሳሌ ነው። ማቴ 17
- የውስጡ አዕማድ የ12ቱ ሐዋርያት ፣ የውጭ አዕማድ የ72ቱ አርድእት

እንዲሁም ወጋግራዎቹ/አዕማዶቹ/ የቅዱሳን መላእክት ምሳሌ ናቸው።

- ትልልቆቹ መስኮቶች የዓበይት ነቢያት ትንንሾቹ መስኮቶች የደቂቀ ነቢያት
- የመቅደሱ 4 ማዕዘን መሆን የአራቱ ወንጌላውያን አንድም የ4ቱ ኪሩቤል ምሳሌ ነው።
- በክብ ቤተ ክርስቲያን ያለው መርገፍ ሄሮድስ ያስፈጃቸው የ14ሺ ሕፃናት ጩኸት ምሳሌ ነው።
- አጸደ ቤተ ክርስቲያኑ፣የቅዱሳን ሰዎች ምሳሌ ነው። ደጀ ሰላሙ የገነት ምሳሌ ነው፣ አጥሩም በሕዝብ ክርስቲያን ይመሰላል።

-- በጉልላቱ ላይ የሰንን እንቁላል መደረጉ - በተፈጥሮ ሰጎን እንቁላል ስትፈለፍል እንደሌሎች የወፍ ዝርያዎች ታቅፋ ሳይሆን ለ40 ቀን ያህል ወንዱና ሴቷ እየተፈራረቁ ትክ ብለው እንቁላሉን በመመልከት/በማየት/ ነው። ነገር ግን ለቅጽበት ዓይናቸውን ቢያነሱ/ቢያዞሩ/ እንቁላሉ ይበላሻል /ይገማል/። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ዘወትር ዓይኖቹ ከቤተ ክርስቲያን እንደማይነቅል ለተወሰነ ጊዜ እኛ ከፊቱ ዘወር ስንል ብንክደው እንደሚያዝንብን እንደሚለየን የሚያሳይ ታላቅ ምሳሌነት ያለው ነው።

1.4 ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊያውቋቸው ፣ሊያደርጓቸውና ሊጠብቋቸው የሚገቡ ሥርዓቶች

- ቤተክርስቲያን ለብሰነው የምንመጣው ነጠላ፣ ሰውነታችን ሁሉ ንጹሕ መሆን አለበት።
- አጭርና ገላን አጉልቶ የሚያሳይ ልብስ ለብሶ መምጣት አይገባም።
- ሴት ስትወልድ ወንድ ልጅ ከወለደች እስከ 40፣ ሴት ልጅ ከወለደች እስከ 80 ቀን ድረስ ወደ ቤተክርስቲያን አትገባም። ከእነዚህ ቀናት በኋላ ግን ገላዋን ታጥባ ትገባለች። ዘሌ 12፥1
- ወደ ቤተ ክርስቲያን ባዶ እጅ መሔድ አይገባም፣ መባዕ፣መሥዋዕት ይዞ መሔድ ያስፈልጋል። ሐጌ 1፥5
- ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ሲደርሱ ማማተብ፣መሳለምና፣መስገድ ይገባል። መዝ 95፥9
- አረማመዳችን በፈሪሃ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እያሰብን ረጋ ብለን መሆን አለበት።
- ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ነጠላችንን አጣፍተን/አደግድገን/መልበስ አለብን።
- ቤተክርስቲያን ውስጥ ተስለው የሚገኙትን የሥላሴ፣የጌታችንን፣የእመበታችንን፣የደጋግ ቅዱሳን ወዘተ... ሥነ-ሥዕላት መሳለምና የአክብሮት ስግደት መስገድ ይገባል። ሮሜ 13፥7

- በቤተክርስቲያን ውስጥ መሳቅ፣መጫወት፣መቀለድ፣መሰዳደብ እንዲሁም ስለ ዓለማዊ ነገር መነጋገር ክልክል ነው። በተለይ በቅዳሴና በትምርት ጊዜ። መክ. 5፥1
- ጠጥቶ/ሰክሮ/ መግባት አይፈቀድም።
- በቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢም ሆነ በአደባባይዋ መሸጥ መለወጥ ክልክል ነው። ማቴ 21፥12
- ጫማ አድርጎ ቤተ መቅደስ መግባት ክልክል ነው። ኢያሱ 5፥15፣ ዘጸ 3፥5
- የሚያኝኮ ቁስል፣የሚነፈርቅ ጉንፋን፣ሳል ተላላፊ በሽታ ያለበት ሰው መግባት ክልክል ነው።
- ለሀጩ የሚዝረበረብበትም ሁሉ አይገባም።
- ሴቶች የወር አበባ ከታያቸው እስከ 7 ቀን ቤተመቅደስ መግባት አይችሉም። ከመቅደሱ ርቀው ግን ማስቀደስ ይችላሉ። በተጨማሪም እምነት መቀባት፣መስቀል መሳለምና የጸሎት መጽሐፍ መያዝ፣መጸለይ/ ይቻላል።
- ባልና ሚስት የመኝታ ግንኙነት አድርገው ሥጋ ወደሙ መቀበል አይችሉም ዘጸ 19፥15
- ወንድ ልጅ ሕልመ ሌሊት/ዝንየት/በመኝታው ከመጣበት በዕለቱ ወደ ቤተ እግዚአብሔር አይገባም፣በማግስቱ ግን ገላውን ታጥቦ መግባት ይችላል።
- በቤተክርስቲያን ውስጥ ወንዶች በሴቶች ሴቶችም በወንዶች መቆሚያ መቀም የተከለከለ ነው።
- ዲያቆን፣ቄስ/ካህን/ ካልሆነ በቀር ከምዕመናን ወገን ማንኛውም ሰው ወደ መቅደስ መግባት ሥጋ ወደሙንም መቀበል አይችልም። 2ኛሳሙ 6፥7-7
- ከቤተመቅደስ የገባና የተቀደሰ ንዋየ ቅድሳትን እንደገና ወደ ውጭ አውጥቶ ለዓለማዊ ነገር ማዋል አይቻልም።
- ኮሶ የታየው ሰው ወደ ቤተመቅደስ መግባት አይችልም።
- ክርስቲያን ከክርስቲያን ጋር ሲገናኝ በተቀደሰ አሳሳም መሳሳም አለበት። ሮሜ 16፥16

ይኸውም፡-

- ካህን ከካህን - እርስ በርስ መስቀላቸውን ተሳልመው ትከሻ ለትከሻ ይሳሳማሉ።
- ምዕመናን ለካህን - ጉልበቱን ስሞ በመስቀል በመባረክ ትከሻ ለትከሻ ይሳሳማሉ።
- ምዕመን ከምዕመን - ትከሻ ለትከሻ መሰሳም /ሠላምታ መለዋወጥ/ አለበት።

ጠቢቡ ሰሎሞን ‹ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባን ጊዜ እግርህን ጠብቅ› /መክ5፥1/ እንዳለ ወደ እግዚአብሔር ቤት /ቤተ ክርስቲያን/ ስንመጣም ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ልናስብና ልንጠብቅ ይገባል።

1.5 ስርዓተ ጸሎት

ጸሎት - ፈጣሪና ፍጡር የሚገናኙበት ረቂቅ መንገድና ልመና እንዲሁም በልመና የሚገኝ ዋጋ ምስጋናም ነው።

በጸሎት አማካኝነት - የእኛን ተገዥነት የእግዚአብሔርን ገዥነት፣የእኛን ተቀባይነት የእግዚአብሔርን ሰጪነት እንረዳለን። በአጭሩ ከእግዚአብሔር የፈለጉትን ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችል መሳሪያ ነው። ማቴ 7፥7 ጸሎትን ያስተማረ አምላካችን እግዚአብሔር ነው። ማቴ 6 ፣ ሉቃ 1፥1-13

ጸሎት - ከፈጣሪ የታዘዘ ሕጋዊ ተግባር መሆኑን የሚያስረዳ በቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ቦታ ተጠቅሷል። ማር 11፥24-26 ፣ ዮሐ 14፥24፣ 1ኛ ተሰ 5፥16

በቤተክርስቲያናችን ጸሎት ራሱን የቻለ አፈጻጸምና ሥርዓት አለው። መቼና በየት መጸለይ እንደሚገባን ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ እንመለከታለን።

1.5.1 . የጸሎት አፈፃፀም ስርዓት

አንድ ክርስቲያን ጸሎት ከመጀመሩ በፊት ምን ማድረግ ይገባዋል

- ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በመዝ 53 ‹... በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ እጠብቃለሁም› እንዳለ ጸሎት ከጀመሩ በፊት መቆም አለበት ይህ ማለት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመቆም የማይችለውን አይመለከትም ሌላው ግን ዓምድ፣ግድግዳ፣ሳይደገፍ፣መቋሚያ ሳይይዝ ቀጥ ብሎ መቆም ማለት ነው።

- ጌታችን በሉቃስ ወንጌል 12፥35 ‹ወገባችሁ የታጠቀ ይሁን ...› ብሎ እንዳስተማረ ጋቢን/ነጠላን/ በመስቀልኛ በማጣፋት መልበስ ይገባል። ፍት.ነገ አንቀጽ 14/
- ፊትን ወደ ምሥራቅ መልሶ መቆም። መዝ 67
- ጸሎት ሲጀመርም ሆነ ሲፈጸም ማማተብ
- የሚጸልይ ሰው በጸሎት ላይ እያለ ጸሎቱን አቋርጦ ከማንም ሰው ጋር ፈጽሞ መነጋገር አይችልም። አሰቸጋሪ ሁኔታ ከተፈጠረ ግን ‹ካቆመበት አቡነ ዘበሰማያት ደግሞ› ጉዳዩን መፈጸም ይችላል።

- ለጸሎት የቆመ ሰው በትሕትናና በጸጥታ ሆኖ ሌላ ሰው እንዳይሰማ /ሌላውን እንዳይረብሽ ሆኖ/ መጸለይ አለበት። 1ኛ ሳሙ 1፥13
- በጸሎተ ማኅበር/በቅዳሴ/ ጊዜ የግል ጸሎት መጸለይ አጥብቆ የተከለከለ ነው።
- ጸሎት ስንጸልይ እጆቻችንን አንስተን ዓይኖቻችንን ገልጠን ወደ ሰማይ በማቅናት መሆን አለበት። መዝ 122፥1፣ ዮሐ 11፥4-1፣ ጢሞ 2፥8

1.5.2 ጸሎትን መቼ እንጸልይ

አንድ ክርስቲያን በቤተክርስቲያን ቀኖና መሠረት በቀን ሰባት /7/ ጊዜ እንዲጸልይ ታዟል። ይኸውም ከማዕድ፣ከጽሎተ ፍትሐት፣ንስሐ ወዘተ ውጭ ነው። ይህ ሲባል ግን ከሰባቱ የጸሎት ጊዜያት ውጭ አምላክ መመስገን አይገባውም ማለት አይደለም። ቢቻል 24 ሰዓት ያለማቋረጥ መጸለይ ይገባል። እንዲያውም የበቁ ቅዱሳን እንደመላዕክቱ ድካም ሳይሰማቸው ሃያ አራት/24/ ሰዓት ሙሉ ጸሎት የሚያደርሱበት ሠዓት አለ። ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በቀን 7 ጊዜ መጸለይ አለብን ያሉበት ምክንያት ምንድነው

1. የቅዱስ ዳዊትን ቃል መነሻ በማድረግ ‹ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ› እንዳለ። መዝ 118፥164
2. ለጸሎት የተጋን እንድንሆን። ሉቃ 18፥1-14
3. ጸሎት የምናደርስባቸው ሰዓቶች ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ስለኛ ብሎ የተቀበለውን ሕማም/መከራና ሞት.../ እንድናስብና እንድናስተውል ብለው ነው።

1.5. 3 ጸሎት በቀን 7 ጊዜ የመጸለያችን ምስጢር

2. በነግህ/12፡00 ሰዓት/፣

- በዕለተ ሰንበት ቅዱሳን መላዕክትን የፈጠረበት ሠዓት በመሆኑ
- አዳም በዕለተ ዓርብ የተፈጠረበት ሰዓት በመሆኑ
- ጌታችንን አይሑድ በምክር ተባብረው ለጲላጦስ አሳልፈው በመስጠት የወሰኑበት ሰዓት በመሆኑ። ማቴ 27፥7

3. ሠለስት/ከረፋዱ 3፡00 ሰዓት፣

- እመቤታችን ብስራተ ገብርኤልን የሰማችበትና ጌታም የተፀነሰበት ሰዓት በመሆኑ

- ጌታችን ይሙት በቃ ተብሎ የተፈረደበትና ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪታይ የተገረፈበት ሰዓት በመሆኑ። ማቴ 27፥3-34
- በዕለተ ሰንበት መንፈስ ቅዱስ ለቅዱሳን ሐዋርያት የወረደበት ሰዓት በመሆኑ። ሐዋ 2፥1-10

4. ቀትር/6፡00 ሰዓት/

- ቅድስት ሥላሴ ለአብርሃም ተገልጠው ቤቱን የባረኩበት ሰዓት ነውና።
- ጌታችን የተሰቀለበት፣የተቸነከረበት፣ልብሱ የተገፈፈበት ሰዓት ነው። ማር 15፥25
- ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትም በዚህ ሰዓት ይጸልይ ነበር። መዝ 54፣17

5. ተሰዓት/9፡00 ሰዓት/

- ጌታችን ቅዱስ ነፍሱን ከክቡር ሥጋው በፈቃዱ የለየበት ሰዓት በመሆኑ። ዮሐ 19፥25-30
- ጌታችን የተሰቀለበት፣የተቸነከረበት፣ልብሱ የተገፈፈበት ሰዓት ነው።

6. ሠርክ/11፡00 ሰዓት/

- ጌታችን ወደ ከርሰ መቃብር የወረደበት ሰዓት በመሆኑ። ሉቃ 23፥50
- አዳም ወደ ገነት የገባበት ሰዓት በመሆኑ።
- በዚህ ሰዓት እስራኤል ዘሥጋ የቁርባን መሥዋዕት ያቀርቡ ስለነበር እኛም የምስጋና መሥዋዕት እናቀርብበታለንና ነው። ዘፍ 29፥39 ዘሌ 6፥20

7. ነዋም/ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት/

- በዚህ ሰዓት ጌታችን ራሱ ጸሎት ለማድረግ ሥርዓተ ጸሎት አሳይቶበታል። መዝ 73፥16 መዝ 4፥8
- አንድ ክርስቲያን ከመተኛቱ በፊት በሰላም ያዋለውን አምላክ አመስግኖ መተኛት ስለሚገባው።

8. መንፈቀ ሌሊት /ከሌሊቱ 6፡00 ሰዓት/

ሀ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት፣ከሞት የተነሣበት፣ዳግም የሚመጣበት ሰዓት ስለ ሆነ። ማቴ 28፥1-10 ሉቃ 2፥1-20 ሉቃ 24፥1-12

ለ. ቅዱስ ዳዊት ይጸልይበት የነበረ ሰዓት በመሆኑ። መዝ 76፥2

ሐ. ቅዱስ ጳውሎስ እና ሲላስ በእስር ቤት ሳሉ ይጸልዩበት ስለነበረ ነው። እኛም እነዚህን ምስጢራትና ኃጢአታችንንም በማሰብ ዘወትር እንድንጸልይ ታዟል። ዕብ 13፥7

1.6 ሥርዓተ አቲብ /የማማተብ ሥርዓት/

ቃሉ አተበ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ማተብ/ማዕተብ/ አመለከተ፣ባረከ፣ቡራኬ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። ማማተብ መባረክ ማመላከት ማለት ነው።

ማማተብ በዘፈቀደ የሚፈጸም አይደለም ስመ ሥላሴን ጠርተን በትዕምርተ መስቀል አመልካች ጣትን ቀጥ አድርጎ ከሌሎች ጣቶች ጋር በማመሳቀል መላ ሰውነትን መቀደስ/መባረክ/ ያስፈልጋል። ስናማትብም ከላይ ወደ ታች ከግራ ወደ ቀኝ በማድረግ ነው። በማማተብ ጊዜም የክርስቶስን መከራ መስቀል ማሰብ ይገባል። ይህን አስበን በእምነት ስናማትብ አጋንንት ከእኛ ይሸሻሉ/ይርቃሉ/ሉቃ 11፥20

1. የማማተብ ትርጉም/ምስጢራዊ ፍቺ/

- በጣታችን ወደ ግምባራችን ማመልከታችን ወይም ለማማተብ መዘጋጀታችን የሥላሴ ልዕልና የሥልጣን ማዕረጋቸውም ከሁሉ በላይ ከፍ ያለ ማንም የማይስተካከለው እንዲሁም የማያልፍ የማይለወጥ ዘለዓለማዊ ዙፋን ያላቸው መሆኑን ለመግለጽ ነው።

ወደ ደረት ማማልከታችን

- ከዓለም መፈጠር በፊት የባህርይ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለየ አካልህ ከሰማየ ሰማያት ወርደህ በማኅፀነ ድንግል ማርያም አደርክ ለማለትነው።

ከግራ ወደ ቀኝ ማመልከታችን

- በሲያል በአጋንንት ሲረገጥ የነበረው አዳምን ከሲያል ወደገነት አገባኸው በማለት
- የአዳም ዘር ሁሉ ከግራ መቆም ወደ ቀኝ መቆም የመመለሱ ምሳሌ ነው።

ከላይ ወደታች ከግራ ወደቀኝ ማማተባችን

- ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ባፈሰሰው ደሙ ድኅነትን እንዳገኘን ዘወትር ለማሰብ
- እባብ ያየ በልጥ በረየ እንደሚባለው ስናማትብ አጋንንት ከእኛ ይርቃሉና ነው።

ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፤ ልብንም ደስ ያሰኛል እንዳለ ቅዱስ ዳዊት መዝ. 18፥8 እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ አድሮ የሠራልን ሥርዓት ግሩምና ድንቅ ስለሆኑ ብንጠብቃቸው ፍጹም ጸጋና በረከት እናገኝባቸዋለን፡፡ የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች እነዚህ ከላይ ከውቅያኖስ በጭልፋ ውኃ እንደመቅዳት ያህል የዘረዘርናቸው ሲሆን ሌሎችም ለአብነትም የጸም ፣የስግደት፣ የመዝሙር ፣የበዓል፣ የቅዳሴ ወዘተ... ሥርዓቶችም እንዳለ ልናስገነዝብ እንወዳለን፡፡

ሥርዓትን መጠበቅና ማክበር እግዚአብሔርን ማክበር ነው፡፡ በአንጻሩ ሥርዓትን አለማክበር ደግሞ እግዚአብሔርን መናቅ ነውና ያስቀጽፋል፡፡ ለእኛ ትምርት ይሆነን ዘንድ ታሪካቸው በ1ኛ ሳሙ 2፥11 ማቴ 4፥1 ዳን 4፥1-31 ማቴ 21፥12 እንደተጻፈው እንደ አፊኒንና ፊንሐስ፣ንጉሥ ብልጣሶር ወዘተ... ያለ ዕድል/ቅጣት/ ሊያገኘን ይችላልና በክርስቶስ በተመሠረተችው በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት የሚኖር ሰው ክብር ለሚገባው ክብርን በመስጠት እንደሚገባ ሆኖ ሊመላለስ ይጠበቅበታል፡፡ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓትና የአምላክን ፈቃድ አክብረን በነፍስ በሥጋችን እንድንጠቀም የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት የሊቀ መላእክት የቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት አይለየን፡፡ አሜን፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2. ሰባቱ /7ቱ / ምስጢራተ ቤተክርስቲያን

እግዚአብሔር አምላክ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ለሰው ልጆች በተለያየ ጊዜ ሲገለጥና ምሥጢራት ሲገለጽላቸው ነበር። በዘመነ ብሉይ በነቢያት አድሮ ሕዝቡ የሚድኑበትን ምሥጢር እንደገለጸ በዘመነ ሀዲስም አንድያ ልጁን ወደ ዓለም በመላክ የተለያየ ምጢራትን በልጁ አማካኝነት ገልጾልናል። ቅድስት ቤተክርስቲያንም የእግዚአብሔር የፀጋው ግምጃ ቤት የምስጢሩ አዳራሽ እንደመሆኗ ልጆችዋ ይህንን የፀጋ ስጦታ እንዲቀበሉ ሰባት ምሥጢራትን አዘጋጅታለች። የምስጢራቱ ባለቤት መስራች ጌታችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የሰባቱ ሚስጥራተ ቤተክርስቲያን አከፋፈል

1. ምሥጢረ ጥምቀት
2. ምስጢረ ሜሮን
3. ምሥጢረ ቁርባን
4. ምሥጢረ ክህነት
5. ምስጢረ ተክሊል
6. ምስጢረ ንስሐ
7. ምስጢረ ቀንዲል

እነዚህ ምስጢራት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ልዩ ፍቅር የገለጠባቸው፤ ሰዎችን ከርኩሰት አንስቶ የቀደሰባቸውና ለክብር ያበቃባቸው መሆናቸውን ተረድተን ልንሳተፍባቸው የተገቡ ናቸው።እነዚህንም በ4 ከፍለን እንመለከታቸዋለን

1. **ለሁሉም የሚሰጡ/የተፈቀዱ/**

- ምሥጢረ ጥምቀት
- ምሥጢረ ሜሮን
- ምሥጢረ ቁርባን
- ምሥጢረ ንስሀ

2. **ተወሰኑ/ለተፈቀደላቸው/ ብቻ የሚፈጸም**

- ምሥጢረ ክህነት
- ምሥጢረ ተክሊል
- ምሥጢረ ቀንዲል

3.**የሚደገሙ**

- ምሥጢረ ቁርባን
- ምሥጢረ ንሰሓ
- ምስጢረ ቀንዲል
- ምሥጢረ ሜሮን

4. **የማይደገሙ**

- ምሥጢረ ጥምቀት
- ምሥጢረ ክህነት
- ምሥጢረ ተክሊል

የሰባቱ ሚስጠራተ ቤተክርስቲያን ትምህርት አስፈላጊነት :- ከእምነት ቀጥሎ በተግባር እንዲፈጸም የታዘዙት እነዚህ 7ቱ ሚስጥራት የሚያስፈልጉት

1ኛ. አዲስ ልደት ከእግዚአብሔር ስለሚገኝባቸው

2ኛ. የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ስለሚያስጡ

3ኛ. የዘለዓለም ሕይወትና የቤተክርስቲያን አባል ስለሚያደርጉ

4ኛ. አንድነትን፣ቅድስናንና የነፍስና የስጋ ፈውስን እንዴት ማግኘት እንደሚገባን መንፈሳዊ እድገት ለሌሎችም መትረፍ የምንችልበትን ትምህርት ስለሚያስገነዝቡ እጅግ ያስፈልጋሉ።

2.1 ምስጢረ ጥምቀት

ይህ ምስጢር ከ5ቱ አዕማደ ምስጢራት አንዱ ሆኖ በሌሎች ትምህርቶች /መፃሕፍት/ የተገለጸ ቢሆንም በዚህ ክፍለ ትምህርት ግን ከስርዓትና አፈፃፀም አንፃር እንመለከተዋለን።

ጥምቀት የቃሉ ፍቺ በውሃ መነከር፣መዘፈቅ ጠልቆ መውጣት ማለት ነው። በቤተክርስቲያናችን በዚህ መልኩ የሚፈጸሙ የጥምቀት አይነቶች

ሀ. **የመታሰቢያ ጥምቀት** - ጥር 11 የምናከብረው የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ያጣነውን ልጅነታችንን ዳግም እንድናገኝ ያደረገበት የእዳ ደብዳቤያችንን የደመሰሰበት ቀን የምናከብርበት በዓለ ጥምቀት ነው። በአጠቃላይ ጥምቀት ክርስትና የተመሠረተበት ቀን ነው። የምንጠመቀውም ለበረከት ነው። ማቴ 3፥16

ለ. **ለፈውስ ጥምቀት** - በተለያዩ ቅዱሳን መካናት ፈልቀው ከደዌ ስጋ የሚፈውሱ ጠበል በድርሳናትና ገድላት ጸሎት ተባርከው ከአጋንንት ቁራኝነት የሚያላቅቁት ጠበሎች ናቸው። 2ኛነገ 5፥1 ዮሐ 5፥2 ዮሐ 9፥2

ሐ. **ማየ ቁደር/የንስሀ ጥምቀት/** -- ሐይማኖቱን ክዶ ከአሕዛብ ጋር ዝሙት ፈጽሞ፣ጠንቋይ ቤት ሄዶ ወዘተ ተጸጽቶ ለተመለሰ የሚፈጸም የጥምቀት አይነት ነው።

መ. የልጅነት ጥምቀት - ዳግመኛ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የምንወለድበትና የልጅነት ስልጣን የምናገኝበት በዚህ አጭር ጽሑፍም ትኩረት የምናደርግበት ነው። ዮሐ 3፥5 ዮሐ 1፥12

ይህ ልጅነት እንበለ ሩካቤ ከእግዚአብሔር በድንግልና የምንወለድበት ነው። በእርግጥም የእግዚአብሔር ልጅ ከመሆን የሚበልጥ ስልጣንና ማዕረግ የለም። ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን ከማለት ውጪ ምን ይባላል።

ለምን ምስጢር ተባለ?

በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ ስለሚኝበት

የሚታየው አገልግሎት፣ ቤተክርስቲያናችን ክርስትና ቤት ብላ በሰየመችው ስፍራ የሚፈጸመው ሥርዓት ነው።

የማይታየው ፀጋ፣ ተጠማቂው ልጅነትን ሲቀዳጅ ስርየተ ኃጢያትን ሲያገኝ በሰው ዘንድ ስለማይታይ ምስጢር ተባለ።

2.1.1 የጥምቀት አመሠራረት

ጥምቀተ ክርስትና የተመሠረተው ጥር 11 ቀን 33ዓ.ም ከለሊቱ 10 ሰዓት በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ነው። ማቴ 3፥16

2›1.1 የጥምቀት አፈጻጸም

መጽሐፈ ክርስትና /ጸሎተ ጥምቀት/ይደገማል

የተሟላ የካህናት ልዑክ ተጠማቂዎችና አቋቋሚዎች በባህረ ጥምቀቱ ዙሪያ ተሰይመው በካህናቱ መሪነት በምዕመኑ ተሳትፎ ጸሎተ ጥምቀቱ ይደርሳል።

የጸሎቱ ዓላማ፣የቀረበውን ውሃ በስልጣነ ክህነቱን በጸሎቱ ወደ ማየገቦ /ከክርስቶስ ጎን የፈሰሰው ውሃ/ለመለወጥ ነው። ዮሐ 19፥34 በዚህ የተጠመቁ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ስልጣን ያገኛሉ የክርስቶስ ቤተሰብ/ክርስቲያን/ ይባላሉ።

በጸሎተ ክርስትናው መገባደጃ ዲያቆኑ የተጠማቂውን አውራ ጣት ይዞ ፀሎተ ሃይማኖት ያስደግመዋል ህፃን ከሆነ የክርስትና አባት/እናት/ የቀኝ እጅ አውራ ጣት በማስያዝ በውክልና እንዲጸልዩ ያስደርጋል ይኸውም ሐይማኖቱን መቀበሉንና ያመነውን መመስከሩን ለማሳየት ነው። ከዚያም ዲያቆኑ ተጠማቂውን ከምእራብ ወደ ምስራቅ ያመጣውና በውሃው አንፃር ያቆመዋል ይኸው የድህነት ተስፋ መሰማቱን ለማዘከር ነው። ድህነት በውሃ ጥምቀት ነውና ከዚያም ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ እንዲቆም ይደረግና ሰይጣንን መካዱን በቃሉ ይመስክራል/ወይም በተወካዩ/ የዳቢሎስን የግዞት ቦታ በስተምእራብ ነውና ከዚያም ወደ ምስራቅ ፊቱን በማዞር በእግዚአብሔር በማመን ይመሰክርና ይጠመቃል ምስራቅ የተስፋ ርስት የገነት ስፍራ መሆኑን ለማጠየቅ ነው።

2.1.2 ጥምቀት በማን ስም

በሥላሴ ስም ሲሆን ሦስት ጊዜ በመጠመቂያው ውሃ ውስጥ እየደፈቁ በማውጣት ይፈጸማል። ይኸውም የሚያመለክተን የአምላክን አንድነትና ሦስትነት፤ የክርስቶስ ሞት

ትንሳኤ በመመስከርና ለመተባበር ነው። ‹የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን› እንዲል ሮሜ 6፥3

2.1.3 ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ

ለወንድ በተወለደ በ40 ለሴት በተወለደች በ80 ቀን ሲሆን በአስገዳጅ ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ይህ ሥርዓት አይሻርም ፍት.ነገ.አን 3 ሥር 2

ከአሕዛብነት/ካልተጠመቁ ወገን/ ለተመለሰው ንዑስ ክርስቲያን በመጣበት የዕድሜ ዘመን ተምሮ ሲየበቃ ይታወቃል። ፍት.ነገ5አን 3 ሥር 2

2.1.4 ሥመ ክርስትና /ሥመ ጥምቀት/

ተጠማቂው ከተጠመቀ በኋላ በዕለቱ ተረኛ ካህን /ሰራዔ ቄስ/ አማካኝነት የተወለደበትን ወይም የተጠመቀበትን ቀን መሠረት በማድረግ ወይም በጥምቀቱ ቀን ሰሞን የዋለውን ዓቢይ በዓል ተንተርሶ የክርስትና ስም ይሰየማል ወልደ አማኑኤል፤ ገብረመድን፣ወለተማርያም፣ማህደረ ማርያም ወዘተ...

ዓላማውም - ኢሳ 56 እንደተገለጸው ቅዱሳንን ለመዘከር የእግዚአብሔር ቤት ነውና

- የክርስቲያንነት መገለጫ መሆኑን ለማስገንዘብ

2.1.5 ማተብ ክርስትና

አማኙ እንደተጠመቀ ማተብ ክርስትና ይደረግለታል አይነቱም ጥቁር፤ቀይ እና ነጭ ክር ሆኖ በአንድ የተገመደ መሆን አለበት።

የዚህ ሚስጢሩም

ጥቁር- አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምክንያት ለማዘኑ/ደግነቱ/

ቀይ - ክርስቶስ ያፈሰሰው ደም ምሳሌ።

ነጩ - ጌታችን ሲጠመቅ በክርስቶስ ላይ ያረፈው የነጩ ርግብ/የመንፈስ ቅዱስ/

ሦስት የመሆኑ፣የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ወይም የሥላሴ ምሳሌ

በአንድ መገመዱ፣ የሥላሴ የአንድ አምላክነት ምሳሌ ነው።

የጥምቀት ጥቅም፣ ለስርየት ኃጢያት

- ልጅነት ለማግኘት
- ለዘላለም ሕይወት

ማተብ ክርስትና ማሠር የተጀመረው በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያዕቆብ ዘእልበረደ በተባለ የእስክንድርያ ሊቀጳጳ አማካኝነት ነው።

2.1.6 አበልጅነት

ትርጉሙ - የክርስትና ልጅ አባት/ሞግዚት/ማለት ነው ይኸውም መንፈሳዊ አባት ወይም እናት ነው።

ዓላማውም - 1ኛ. መንፈሳዊ ዝምድናን ለመመስረት ሲሆን ጋብቻን ይከለክላል

2ኛ. የመጋቢነት ኃላፊነትን ለመስጠትነው።

የክርስትና አባት/እናት/ የሚሰጠው ለማን ነው

1ኛ. ለግለሰብ ሲሆን መስፈርቱም

- ራሱን ማስተዳደር የሚችል
- መንፈሳዊ እውቀት ያለው
- ክርስትናን መኖር በመረጡ ቤተሰቦች መካከል ሕፃንም ቢሆን

2ኛ. ለታቦት፣ቤተክርስቲያን እንዲማር እንዲያገለግል ለማድረግ

2.1.7 በክርስትና ጊዜ የሚደረገው

መሠረቱ በሉቃ 15 ተመዝግቦ የምናገኘው የጠፋው ልጅ ታሪክ ሲሆን በተጨማሪም ‹በአንድ ኃጢአተኛ ንስሀ መግባትና ልጅነት ማግኘት በሰማይ መላእክት ዘንድ ደስታ ይሆናል›እንዳለ ሉቃ 13÷1 ለተጠማቂው አዲስ ልብስ ማልበስ አቅምን ያገናዘበ ጠበል ጸዲቅ/ድግስ/ በማዘጋጀት አዳምና ሄዋን በተፈጠሩ በ40 ና በ80 ቀናቸው በመላእክት ታጅበው ወደተድላ ገነት እንደገቡ ተጠማቂውም በአቋቋሚዎች ታጅቦ በዝማሬ በእልልታ በደስታ በዓሉ ይከበርለታል። ኩፋ 4÷9

2.2. ምስጢረ ሜሮን

ትርጉም

ሜሮን ቃሉ የግሪክ ሲሆን ቅዱስ ዘይት/ቅባት/ይባላል የሚጣፍጥ ሽታ ያለው የተቀመመ ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲያያዝ የመጣ የተባረከና የተከበረ ዘይት ነው።

ስለምን ምሥጢር ተባለ

ጥምቀተ ክርስትናን የፈጸመ ምዕመን በካህኑ አማካኝነት ሜሮኑን ሲቀባ ቢታይም የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ሲቀበል ስለማይታይ ነው።

2.2.1 አመሠራረት

የቅዱስ ዘይት ስርዓት ከጎገ ልቦና ጀምሮ የነበረ ሲሆን አገልግሎቱም ሐብተ መንፈስ ቅዱስ ማሳደር ነው። ዘጸ 30÷22-25 1ሳሙ 16÷1 ቅዱሳን ሐዋርያትም ከርዕሳነ አበው የተማሩትን /የነበረውን ስርዓት/ ጠብቀው ይገለገሉበት ነበር ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንም እስከ አለም ፍፃሜ ለአገልግሎቱ ምቹ መሆን በመረዳት ፀጋ እግዚአብሔርን ለማሰጠት ስርዓቱ በሜሮን እንዲሆን በመደንገግ ከዘመናችን ደርሷል።

- በሐዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ጌታችን ከትንሳኤው በኋላ በደቀመዛሙርቱ በእሳት አምሳል አሳድሮባቸዋል። ሉቃ 24 ሐዋ 1
- ቅዱሳን ሐዋርያትም ቁጥራቸው ጥቂት በነበሩ ክርስቲያኖች እጅ በመጫን ያሳድሩ ነበር። ሐዋ 8÷14-17 ሕዋ 19÷5-6

- ክርስቲያኖች እየበዙ አገልግሎቱም እየሰፋ ሲሄድ በዓለም ሁሉ እየዞሩና እያጠመቁ ሁሉንም እጅ በመጫን ፀጋውን ለማሳደር እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ብዙ ተቃዋሚዎች/ ዓላውያን ነገስታት/ ክርስቲያኖችን የሚያሰቃዩ ስለነበሩ ጊዜውን ስለመሻማት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በሲኖዶስ ደረጃ /ጳጳሳቱ/ ተሰብስበው በዘይቱ ላይ እጃቸውን በመጫን ሃብተ መንፈስ ቅዱስን

ካስተላለፉ በኋላ በየአብያተ ቤተክርስቲያናቱ በማከፋፈል አገልገሎቱ በቀሳውስት እንዲፈጸም ስርዓት ሠርተዋል።

- በተጨማሪም ጌታ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ነጭ ርግብ እንዳረፈበት ተጠማቂውም ሳይውል ሳያድር ፀጋውን መቀበል ስላለበት ነው።

2.2.2 ምስጢረ ሜሮን ትንቢትና ምሳሌ

ምሳሌ ዘፍ 28፡1-32 የሰፈረው የያዕቆብ ታሪክ የሚስጥረ ሜሮን ምሳሌነው ይኸውም

- ያዕቆብ -የጳጳስ
- ዘይቱ - የቅብዐ ሜሮን
- ድንጋዩ - የቤተክርስቲያን
- የአሕዛብ

2.2.3 የምሥጢረ ሜሮን ጥቅምና ዓላማ

- ፀጋ መንፈስ ቅዱስን ያሳድራል
- ልጅነትን ያድለናል/የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ነው/ ወይም በጥምቀት የተገኘውን ዳግም ልደት ያረጋግጣል።
- ለአዲስ ሕንፃ ቤተክርስቲያን እና ለነዋያት ማክበሪያ ይውላል
- ሥልጣነ ክህነትንና ተክሊልን ያጸናል
- ለነገስታት የሹመት ማክበሪያ ሆኖም ያገለግል ነበር

ዓላማው - እግዚአብሔር ጸጋውን የሚሰጥበት ዓላማ

1ኛ. እርሱ ለሚከብርበት ሕይወት እንድናውለው

2ኛ. ሰዎችን ወደ ፈጣሪያቸው ለማቅረብ

3ኛ. በዚህ ዓለም እንድንኖርበት ይሄ ለሚያምንም ለማያምንም ይሰጣል ::

2.2.4 አዘገጃጀት

ቅብዓ ሜሮን በገሊላና በይሁዳ ይልቁንም በኢያሪኮ የሚበቅል ከሽቱ እንጨቶች ሁሉ ከሚበልጥ በለሳን ከተባለ ዛፍና ልዩ ልዩ ጣዕም ካላቸው ከ40 በላይ የሽቱ እንጨቶች ተቀምሞ የሚዘጋጅ ቅዱስ ቅባት ነው።

- አንድም ፍትሐ ነገስት የጌታ ወዝ/ላብ/ በፈሰሰበት ቦታ የበቀለ እንጨት ነው ይለዋል/በለሳንን።/
- የሚዘጋጀውም በጳጳሳት ሲሆን እንጨቱ ተቀቅሎ ይጨመቅና በአለሙት ይኸውም በንፍሐትና በአንብሮተ እድ ይከበራል የኢት/ኦ/ተ/ቤተ/ክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከግብጽ ነበር ሜሮኑን የምታመጣው አሁን ግን ራሷ ታዘጋጃለች።

ካስተላለፉ በኋላ በየአብያተ ቤተክርስቲያናቱ በማከፋፈል አገልገሎቱ በቀሳውስት እንዲፈጸም ስርዓት ሠርተዋል።

- በተጨማሪም ጌታ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ነጭ ርግብ እንዳረፈበት ተጠማቂውም ሳይውል ሳያድር ፀጋውን መቀበል ስላለበት ነው።

2.2.2 ምስጢረ ሜሮን ትንቢትና ምሳሌ

ምሳሌ ዘፍ 28:1-32 የሰፈረው የያዕቆብ ታሪክ የሚስጥረ ሜሮን ምሳሌነው ይኸውም

- ያዕቆብ -የጳጳስ
- ዘይቱ - የቅብዐ ሜሮን
- ድንጋዩ - የቤተክርስቲያን
- የአሕዛብ

2.2.3 የምሥጢረ ሜሮን ጥቅምና ዓላማ

- ፀጋ መንፈስ ቅዱስን ያሳድራል
- ልጅነትን ያድሰናል/የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ነው/ ወይም በጥምቀት የተገኘውን ዳግም ልደት ያረጋግጣል።
- ለአዲስ ሕንፃ ቤተክርስቲያን እና ለነዋያት ማክበሪያ ይውላል
- ሥልጣነ ክህነትንና ተክሊልን ያጸናል
- ለነገስታት የሹመት ማክበሪያ ሆኖም ያገለግል ነበር

ዓላማው - እግዚአብሔር ጸጋውን የሚሰጥበት ዓላማ

1ኛ. እርሱ ለሚከብርበት ሕይወት እንድናውለው

2ኛ. ሰዎችን ወደ ፈጣሪያቸው ለማቅረብ

3ኛ. በዚህ ዓለም እንድንኖርበት ይሄ ለሚያምንም ለማያምንም ይሰጣል ::

2.2.4 አዘገጃጀት

ቅብዓ ሜሮን በገሊላና በይሁዳ ይልቁንም በኢያሪኮ የሚበቅል ከሸቱ እንጨቶች ሁሉ ከሚበልጥ በለሳን ከተባለ ዛፍና ልዩ ልዩ ጣዕም ካላቸው ከ40 በላይ የሸቱ እንጨቶች ተቀምሞ የሚዘጋጅ ቅዱስ ቅባት ነው።

- አንድም ፍትሐ ነገስት የጌታ ወዝ/ላብ/ በፈሰሰበት ቦታ የበቀለ እንጨት ነው ይለዋል/በለሳንን።/
- የሚዘጋጀውም በጳጳሳት ሲሆን እንጨቱ ተቀቅሎ ይጨመቅና በጸሎት ይኸውም በንፍሐትና በአንብሮተ እድ ይከበራል የኢት/አ/ተ/ቤተ/ክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከግብጽ ነበር ሜሮኑን የምታመጣው አሁን ግን ራሷ ታዘጋጃለች።

2.2.5 አፈፃፀም

ቡብሉይ ኪዳን - በመቀባት
በሐዋርያት ዘመን - እጅ በመጫንና በመቀባት
በዘመናችን - በተመሳሳይ

ማንኛውም ተጠማቂ ከጥምቀት ቀጥሎ የሚፈጸመው ይህ ምሥጢር ሲፈጸም በጳጳስ ወይም በቄስ አማካኝነት 36 የሰውነት ክፍል እንዲቀባ ሥርዓት ያዝዛል። ሲቀባም ስመ ክርስትናውንና የሚቀባውን የሰውነት ክፍል እየጠራ ነው።

ተጠማቂዋ አዋቂ ሴት ከሆነች፣ 60 ዓመት በሞላት ወይም ቤተክርስቲያን ለዚህ ስርዓት ባዘጋጀቻት ሴት ዲያቆናዊት አማካኝነት የካህኑን ጣት/እጅ/ በመያዝ ዲያቆናዊቷ ትቀባታለች ይኸውም ካህኑን ከፈተና ለመጠበቅ ምዕመኗም እንዳታፍር/እንዳትሰናከል/ ነው።

በአሁን ጊዜ በጥምቀተ ክርስትና ወቅት ከላይ በገለጸው መልክ ሳይሆን ቅብዓ ሜሮኑን ማየገበው ውስጥ በመጨመር መላ አካሉን ቅባቱ እንዲደርሰው በማድረግ ተጠምቆ ሲወጣ ለምልክት ብቻ ፊቱን እጁንና እግሩን ይቀባል።

2.2.6 ቤተክርስቲያን ፀጋ መንፈስ ቅዲስን የምታሳድረው በምንድን ነው

- በሜሮን፣ከላይ ‹ጥቅም› የሚለው ንዑስ ርዕስ ላይ እንደገለጸው ተጠማቂው በቅብዓ ሜሮን/በተቀደሰው ዘይት መቀባት/ አማካኝነት ፀጋ እንዲያድርበት ያደርጋል።
- በአንብሮተ እድ/እጅን በመጫን/ ይህ ሥርዓት ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ ሲተላለፍ የደረሰ ነው። ዛሬም ቤተክርስቲያን ካህናትን ጳጳሳትን ሥትሾም ወዘተ እጅ በመጫን ፀጋን ታሳድራለች፡
- በንፋት/እፍ በማለት/ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ በካህናቶች አማካኝነት ታሳድራለች መስራቹም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

2.2.7መንፈስ ቅዱስ በሰው ላይ ሲያድር ምልክቱ ምንድን ነው

መንፈስ ቅዱስ ከእናት ማህጸን ጀምሮ ያድራል ነገር ግን ጸጋውን ሲያሳድር አይታይም የሚታወቀውም

1ኛ. እግዚአብሔር ፈቅዶ ሲገልጠው ይኸውም ከመደበኛው ሰው ተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ ለአብነት ዓድቁ ተክለሀይማኖት/መጥምቁ ዮሐንስ፣ቅ.ቂርቆስ፣ሐዋርያት ወዘተ....

2ኛ. የክርስቱያኑ መንፈሳዊ ሕይወት እያደገ ሲመጣ በውስጡ የታመቀውን ጸጋ በሚያሳየው ትጋት ሲገለገልበት/ማለትም በልምምድ/ ለአብነት የቅዱሳንን ሕይወት መመልከት ይቻላል ቀስ በቀስ ሙት የማስነሳት/የተሰወረውን የማወቅ የማስተማር ወዘተ... ብቃት ላይ የደረሱ በርካታ ናቸው።

2.3 ምስጢረ ቁርባን

ትርጉም - ቁርባን አምሃ/ስጦታ/፣መስዋት ማለት ነው
ስጦታነቱ - እግዚአብሔር ለሰው ያቀረበው ስጦታ አንድያ ልጁን በመሆኑ ዮሐ 3፥16 አንድም ሰው ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው መስዋዕት መቅረቢያ ሆኖ ቁርባን ይባላል።

ስለምን ምስጢር ተባለ?

ህብስቱና ወይኑ ወደ ፍፁምና እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም ሲለወጥ ስለማይታይ። ካህኑ 13 ቦታ ሲፈትተው ሲፀልይበት ይታያል።

2.3.1 አመሠራረት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕማማቱና ከሞቱ በፊት ሐሙስ ምሽት በ34ዓ.ም በአልአዛር ቤት ነው የመሠረተውም ይኸውም የኦሪቱን መስዋት ከበሉ በኋላ ያንን በተአምራት ከሆዳቸው አጥፍቶ አዲሱን ኪዳን መቀበላቸውንውን ሕብስቱንና ወይኑን በመለወጥ እውነተኛ ሥጋና ደም አድርጎ ሰጥቷቸዋል።

3.2.2 አዲሱ ኪዳን/ውል/ ምንድን ነው

ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ‹ የሚል ሲሆን ይህን በበላንና በጠጣን ጊዜም ሞቱን እንድናስብ አዝዞናል ስለዚህም ቤተክርስቲያን ዘወትር በቅዳሴዋ ‹ንዜኑ ሞትከ ወነአምን እርገተከ... እያለች ታስባለች።

3.2.3 የቁርባን ጥቅም

- ከነፍስ ረሃብና ጥም የምንድንበት መንፈሳዊ ምግብ ነው ዮሐ 6፥35
- ሥርየተ ኃጢያትን የምናገኝበትነው ማቴ 26፥27
- የቅዱሳን ሕብረትን በመንፈስ እናገኝበታለን 1ቆሮ 10፥16-18
- የዘለአለም ሕይወት እናገኝበታለን ዮሐ 6፥54

3.2.4 ምስጢረ ቁርባን በስርዓተ ቅዳሴ

ቅዳሴ ማለት - ከምስጋና ሁሉ የሚበልጥ ምስጋና ማለት ነው። ይኸውም ሕብስቱንና ወይኑን ወደ ፍፁም ሥጋና ደም ለመለወጥ የሚደረግ ጸሎት ነው።

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ተወልዶ ቀራንዮ እስከተሰቀለበት ድረስ በእንቅስቃሴ /በድርጊት/ እና በንባብ የሚደረግ ጸሎት ሲሆን በውስጡም ጸሎተ ፈትሀት፣አኩቴተ ቁርባን ወዘተ.... የተባሉ የጸሎት ሥርዓትን ያካተተ ነው።

የምዕመናን ሱታፌ

- ግብር ማግባት፣ለቅዱስ ቁርባን የሚሆነውን ንጹህ ስንዴ፣ዘቢብ/ወይን/፣እጣን ወዘተ..
- በንስሀ ተመልሶ ለቁርባን መዘጋጀት
- በፍፁም ንቃት ተሰጥኦውን በመመለስ ማስቀደስ

ድርጊት ምንድን ነው

ብዙ ጊዜ ከእግዚአታ ቀጥሎ ድርገት ወረደ ሲባል ይስተዋላል ይሄ ማለት ጌታችን ከሰማያት መውረዱን ሞቶ ተነስቶ ማረጉን የሚያሳይ ሥርዓት ሲሆን ሥጋወደሙ ከመቅደስ ወደ ቅድስት መውረዱን ድርገት ወረደ ሲባል ሲመለስ/ሲያርግ/ ደግሞ ድርገት ተመለሰ ይባላል።

3.2.5 የሥርዓተ ቁርባን አቀባበል ቅደም ተከተል

ጳጳሳት፣ቆሞሳት፣የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ፣አበምኔት እመምኔት/ ቀሳውስት፣ዲያቆናት፣ሌሎችም በየማዕረጋቸው በተክሊሊ የሚጋቡ ሙሽሮች፣ክርስትና የሚነሱ ህፃናት፣የካህናት ሚስቶች፣ ምዕመናን ወንዶች፣ሴቶች አረጋውያን ወራዙት/ወጣቶች/ በቅደም ተከተል ይቆርባሉ።

የቅዳሴ ጠበል ለምን

1ኛ. ለቆረበ ሰው ብቻ የሚሰጥ አለ

2ኛ ኃጢያት ሲበዛ ቆራቢ ሲጠፋ ከዚህ ሚስጥር የራቁት ለማቅረብና ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማድረግ ሙሉ ቅዳሴውን ለተሳተፉም በልዩ ሁኔታ ይሰጣል።

3.2.6 ለቅዱስ ቁርባን የሚደረጉ ጥንቃቄዎች

ሀ. ቅድመ ቁርባን

- ንስሀ መግባት
- ሰውነትና ልብስን ንጹሕ ማድረግ
- 18 ሰዓት መጾም/ለአዋቂዎች
- ቤተ መቅደስ መግባት የሚከለክሉትን ማክበር። ለምሳሌ፣ ከሰውነቱ ፈሳሽ የሚወጣበት ጉንፋን የያዘው፣በዝንየት የተመታ ወዘተ...

ለ. ጊዜ ቁርባን/በቁርባን ጊዜ/

- ሙሉ ቅዳሴን መካፈል
- አፍን በነጠላ መሸፈን ተሃዋሲያን እንዳይገቡ
- በተሰበረ ልብ በትህትና ኃጢያተኛነትን እያመኑ የእግዚአብሔር ቸርነት እያሰቡ መቅረብ
- ተራን ጠብቆ ከመጋፋት ተቆጥቦ መቅረብ

ሐ. ድህረ ቁርባን

- ተሃዋሲያን እንዳይገቡ አፍን መሸፈን
- አለመራቆት፣አለመታጠብ
- ንጽህናን፣ቅድስናን ጠብቆ መኖር ወዘተ..

2.4. ምስጢረ ክህነት

ትርጉም - ካህን አገልጋይ ማለት ነው። ዮሐ 20፥21-23
-ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ

- ሚስጥራተ ቤተክርስቲያንን ፈፅመው የሚያስፈፅሙ
- ከራሳቸው ይልቅ ለሌሎች ጥቅም የሚተጉ

- ለእርሱና ለመቅደስ አገልግሎት የተመረጡ/የተለዩ/ ናቸው
- ለራሳቸው ብቻ ከሆነ ማመንና ሚስጥራትን መፈጸም በቂያቸው ነው።

ስለምን ምሥጢር ተባለ?

የማሰር የመፍታት ሥልጣን ከእግዚአብሔር ሲቀበል በዓይነ ስጋ ስለማይታይ 2ጢሞ 1፥6

2.4.1 አመሰራረት - ክህነት በብሉይና በሐዲስ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን

- ካህናትን/አገልጋዮቹን/ የሚመርጥ የሚሾም ሥርዓቱንም ያሳየ እግዚአብሔር ነው ዘኁ 1፥50
- የመጀመሪያው የክህነት ምርጫ የተደረገው በፈጣሪ ፈቃድ ከ12ቱ ነገደ እስራኤል መካከል ሲሆን የሌዊ ነገድ ነው የተመረጠው ዘኁ 17፥1-11

ከሌዊም ነገድ የመጀመሪያው ሊቀ ካህን አሮን ነው ዘኁ 1፥50 ፣ ዘኁ3፥5 ኢያሱ 14፥4 ዕብ 6፥10

የብሉይ ኪዳን ካህን አገልግሎቱ

- የመቅደስ አገልግሎት ያከናውናል፣ይጸልያል፣መስዋት ያቀርባል፣ ይቀባል
- በዓመት አንዴ የራሱንና የሕዝቡን ኃጢያት ያስተሰርያል
- ሕጉን ያስፈፅማል
- ክህነቱ ፈፁም አይደለም/ከሞት አያድንም/ምክንያቱም ባለዕዳ ስለሆነ ነው

2.4.2 በሐዲስ ኪዳን

‹እኔ ኦሪትንና ነቢያትን ልሽር አልመጣሁም› ያለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሊቀ ካህናት በመሆን ሚስጥረ ክህነትን መስርቶታል። ሐዋ 6፥1-6፣ሐዋ 14፥21 ቲቶ 1፥4-9 ማቴ 28፥20 ሉቃ 6፥12-13 ሌሊቱን ሲጸልይ አድሮ ከተከታዬቹ መካከል 12ቱን ደቀ መዛሙርት መርጦ ሐዋርያት ብሎ ስይሚቸዋል ለእነርሱም ማቴ 16፥16-20 የመንግስተ ሰማያት ቁልፍ የማሰር የመፍታት ሥልጣን ሰጥቷቸዋል ማቴ 10፥1-8 ማቴ 18፥18 በአጋንንት፣ለደዌያትና በሞት ላይ

ሾሚቸዋል ሐዋ 20፥17-28 በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ትጠብቋዋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ በሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ሲልም ቤተክርስቲያንን የማስተዳደር ኃላፊነት ሰጥቷቸዋል።

ጳጳስ፣ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉመም የበላይ ተመልካች፣ባለአደራ ማለት ነው።

2.4.3 ሥልጣነ ክህነት ለማን

ሥልጣነ ክህነት ለሁሉም አይሰጥም አንድ አገረ ገዢ/ንጉስ/ ሥልጣኑን ለሁሉም እንደማይሰጥ ለዚህም ከላይ የጠቀስነው የአሮንና የሐዋርያት መመረጥ በቂ ማስረጃ ነው። ጌታችንም ከ12ቱ ደቀ መዛሙርት ቀጥሎ 72ቱን አርድዕት 36ቱን ቅዱሳት አንስት እየመረጠ ነው ያሳየን።

2.4.4 የክህነት መስፈርት

1. የሐይማኖት ትምህርት የተማረ 1 ጢሞ 3፥1-13፣ 1ጢሞ 5፥22
2. በመልካም ጠባዩና አኗኗሩ የተመሰከረለት እንዲሁም ቤተሰቡን ለማስተዳደር የሚበቃ
3. ምስጢራትን ያጠናቀቀ/ያወቀ/ ወይም ለዲቁና እና ለቅስና የሚያበቃውን ትምህርት የተማረ
4. የስጋም የነፍስም ንጽህናውን የጠበቀ/ድንግል/
5. ከሚስጥራት የሚሳተፍ
6. ለማስተማር፣የምዕመናን ኖላዊ ለመሆን የሚበቃ
7. ሚስጥር የሚጠብቅ/የታመነ/ መሆን አለበት

በቤተክርስቲያን ሥርዓት ሥልጣነ ክህነት ለሴትም ይሰጣል። የአገልግሎት ድርሻዋና መስፈርቱ ግን ይለያል

መስፈርቱ

- 60 ዓመት የሞላት

- በእምነቷና በምግባርዋ የተመሠከረላት
- በአንድ ባል የጸናች ወይም በድንግልና የጸናች። ቲቶ 2፥3 1ጢሞ 5፥9

አገልግሎቷም፣ ለመገበርያ የሚሆነውን ታዘጋጃለች

- ከሴቶች መቆሚያ በኩል ስርዓትን ታስጠብቃለች፣ትመክራለች ፣ ትረዳለች
- የካህኑን እጅ ይዛ ሜሮን ትቀባለች
- ጉዳይ ያላቸውን ወደቄሱ/ጳጳስ/ ታቀርባለች

አንዳንዶች 1ጴጥ 2፥9-10 ‹እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉስ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ በርሱ የተለየ ወገን ናችሁ እናንተ ደግሞ ወንን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ እናንተ ምህረት

ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምህረትን አግኝታችኋል› ተብሎ የተፃፈውን በመያዝ ማንም አማኝ ወንድም ሴቱም ካህን መሆን ይችላሉ ይላሉ ነገር ግን ይህ ቃል በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው በሥጋወደሙ የከበሩ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን በጎነትና ምህረት ለሚያምኑ ወገኖች እንደ ካህናትና

መምህራን ሆነው እንዲናገሩ እንዲመሰክሩ በመልካም አርአያነታቸውም የእግዚአብሔርን ስም እንዲያመሰግኑ የተነገረ ቃል ነው።

2.4.5 የካህን ተግባራት

1. ሂዱና አስተምሩ የሚለውን የወንጌል ቃል በመፈፀም ማቴ 28፥19
2. በጸሎት መትጋት ሐዋ 6፣1-4 ሰውን ከእግዚአብሔር ማስታረቅ 2ቆሮ 5፥18-21
3. የህዝብን ኃጢአት ለማስተሰረይ እና የቅድስና ጎዳና ለማስተማር ዮሐ 20፥23 1ጴጥ 1፡17 እንዲሁም ሚስጥራተ ቤተክርስቲያን ለመፈጸምና ለማስፈጸም
4. ሕዝበ ክርስቲያንን ለመጠበቅ በጎቼን ጠብቅ ተብለዋልና ዮሐ 21፥15-17 ከነጣቂ ተኩላ፣ከመናፍቃን፣ከዲያቢሎስ ወጥመድ ማስተማር፣መገሰጽ/መጠበቅ

ለዚህ ሐዋርያዊ ሥራቸው የምዕመናን ትብብር ያስፈልጋቸዋል።

2.4.6 የካህን ማዕረጋት

ጠቅለል ባለ መልኩ ክህነተ ማዕረግ በ3 ይከፈላል እነርሱም

1. ኤጲስ ቆጶስ/ጳጳሳት/ በሐዋርያት ወንበር የሚሰጥ፣ሥልጣኑ ምሉዕ ነው። በቤተክርስቲያን ሥልጣኑ ከፍተኛ ነው።
   - ቀሳውስትና ዲያቆናትን ይሾማል/በአንብሮተ ዕድ/
   - ሜሮን ይባርካል፣አዲስ ቤተክርስቲያን እና ነዋያቱን ይባርካል 1ጢሞ 1፥7-9
2. ቄስ ክህነት ከመስጠት ውጪ ያሉትን 6ቱን ሚስጥራተ ቤተክርስቲያን ይፈጽማል አበ ነፍስና የምዕመናን ቅርብ ነው
3. ዲያቆን የጳጳሱና የቄሱ ረዳት ሆና ያገለግላል
   - ሥርዓትን ያስጠብቃል
   - ቅዱሳት መፃፍትን ያነባል
   - የያስተምራል ይሰብካል ወዘተ...

2.4.7 ካህናትን ማክበር ይገባል

1. የኦሪት ሕግ - አባት እናትህን አክብር ስለሚል ዘጸ 20
2. እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማክበር ስለሚገባ መዝ 14፥1
3. ለቀሳውስት ይልቁንም ለመምህራን እጥፍ ክብር ይገባቸዋል ስለሚል 1ጢሞ 5፥17 አክብሮታችንን የምንገልጽበት፣ በመታዘዝ፣በሚያስፈልግበት መርዳት ወዘተ.... ነው።
   በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሚስጥረ ንስሀ ትምህርት ላየ የካህኑና የንስሀ ልጅ ግንኙነት የሚለው ንዑስ ርዕስ በመመልከት የበለጠ መገንዘብ ይቻላል።

2.5 ምስጢረ ተክሊል

ይህ ምስጢር ታላቅ ነው ኤፌ 5፣31-32

ትርጉሙ ተክሊል ተከለለ፣ተቀዳጀ፣ተሸለመ/የሰማእትነት ዋጋ ተቀበለ ማለት ነው።

ስለምን ምስጢር ተባለ

በሚታይ አገልግሎት የማይታይ የአንድነት ጸጋ ስለሚያስገኝ ነው።

የሚታየው አገልግሎት ሙሽራውና ሙሽሪት ጸሎተ ተክሊሉ ሲደርስላቸውና ተክሊሊ ሲቀናጁ ሲቆርቡ ይታያል።

የማይታየው ጸጋ፣ ሁለቱ ጥንዶች በግብረ መንፈስ ቅዱስ የአንድነት ጸጋ ሲያኙ አይታይም

2.5.1 አመሠራረት

ጋብቻ የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ነው። የመሠረተውም እርሱ ነው። ዘፍ 2፥24 ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ስለዚህ የምትመቸውን እረዳት እንፍጠርለት እንዲል አዳምን ከፈጠረ በኋላ የማትቆረቁረውን የራሱን አካል ፈጥሮ ሚስት እንድትሆነው ሰጠው ዮሐ 2፥1-11 በዘመነ ሥጋዌ ጌታችን የመጀመሪያ ተአምሩን ያደረገውና የባረከው ጋብቻን ነበር።

ምስጢረ ተክሊል ምንድነው

1. የሙሽራውና የሙሽራይቱን የጋብቻ ቃልኪዳን በኃይማኖት የሚያጸና የጸሎት ሥርዓት ነው።
2. የጋበቻ ግዴታን ለመወጣት የሚያስችል መተሳሰሪያ ነው።
3. በፍቅርና በመተማመን የሚያስተሳስር ሚስጥር ነው።
4. ቅድስናንና ዘላቂ አንድነትን የሚያስገኝ ሆኖ ከቁርባን ጋር የሚሰጥ ምስጢር ነው።

2.5.2 የጋብቻ ዓላማ

ዘርን ለመተካት- ዘፍ 1፥27

- የተመሳሳይ ዖታ ጋብቻ የሚፈጽሙ ከእግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ውጪ የሆነና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን እግዚአብሔር ፈቃዱን ስላልፈጸሙ ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ነውረኞች ናቸው
- እንደ አውናንም ዘር ላለመተካት ዘራቸውን ወደ ውጪ የሚያፈሱም አሉ። በጋብቻ ውስጥ ሆኖ ይህን ድርጊት መፈጸም ያስጠይቃል።
- ዘሩን/ልጁን/ ፈልገው አብሮ መኖርን የማይፈልጉም አሉ
-

ለመረዳዳት- /ዘፍ 2፥18 1ቆሮ 7፥1-10

- በመንፈሳዊ ህይወት
- በሐሳብ
- በሥራ/በኢኮኖሚ/

- በመኻታ
- በሁሉም ነገር

- ከላይ በቁጥር 1 እንደገለጽነው ልጅ/ዘር/ፈልገው መረዳዳቱንና አብሮ መኖሩን ማይፈቅዱም አሉ።

- የመረዳዳትን ትርጉም ባለመረዳት በአስተዳደግ ችግር በግልጽነት መጉደል ወዘተ... ለፍቺ የሚዳረጉ በርካቶች አሉ
- መረዳዳት ሲባል ከእርስ በርስ ባሻገር አቅም እስከ ፈቀደ ድረስ እስከ ቤተሰብ/ወላጆቻቸው/ ድረስ ይደርሳል።

ከዝሙት ለመጠበቅ - ማቴ 19፥10 1ቆሮ 7፥8-9

- በእጮኝነት ጊዜ ለመጠናናት በሚል ሰበብ ወደዚህ ሕይወት የሚገቡ አሉ
- ምንም እውቅት ሳይኖረው እንዲሁ አብረው የሚኖሩ አሉ ይኸውም ሥጋ ፈቃድን ለመፈጸም ብቻ
- ባለመጣጣም ሰበብ ሰነፈች መክነች ብዬ ላለተዋት ብለው በእግዚአብሔር ፊት የገቡትን ቃልኪዳን የሚያፈርሱም አሉ ይህ ስህተት ነው። ሁለት ባልና ሚስት በመኻታ ተዋውቀው ዘር ተካፍሎ ፍሬ እስከተገኘ ድረስ ሩካቤ ተፈጽሚልና በቂ ነው። መታገስ መደጋገፍ ያስፈልጋል እንጂ እርካታ አጣው በሚል ጋብቻን ማፍረስ ከባድ ነው። አልበላሁም እና አልጠገብኩም ይለያያሉ ጌታችንም በወንጌል በራስ ላይ ቢደረግ የማትወደውን በወንድምህ ላይ አታድርግ ይለናል።

የቅዱስ ጋብቻ ጥቅም

- በስጋ ወደሙ ለጸኑ በሰማይም በምድር ክብርና በረከት ያሰጣል
- የተቀደሱ ልጆች ይገኙበታል
- መተማመንና በአንድነት መጽናትን ያስገኛል
- ከኃጢያት ጠብቆ ይቀድሳል ዕብ 13፥4

2.5.3 ሥርዓተ ተክሊል ለማን ፍት ነገ፣አን 24/899

- ለደናግላን ብቻ
- አንዳቸው ድንግል ሌላኛው ፈት/የሌላቸው/ቢሆኑ ሁለቱ በተስማሙበት ይፈጸምላቸዋል። ማለትም ድንግልናውን የጠበቀው ቢፈልግ ብቻውን ተክሊል ይቀዳጃል ካልሆነም በመአሰብ መፈጸም ይችላል ዮሐ 13፥34-35
- ሁለቱም ፈቶች/መዓሰባን/ ድንግልና የሌላቸው ከሆነ ፍትሀ ዘወልድ ብቻ ተደግሞላቸው በሥርዓተ ቁርባን አንድ መሆን ይችላሉ።

2.5.6 የተክሊል ስርዓት አፈፃፀም

1. ቅድመ ተክሊል፡-

- ስለ ምስጢረ ተክሊል በቂ ትምህርት መማር
- የስጋና የነፍስ ንፅህናን መጠበቅ
- አዲስ (ንፁህ)ልብስ ማዘጋጀት
- ለቅዱስ ቁርባን የሚደረጉ ጥያቄዎችን መፈፀም
- ሚዜዎችም ቢሆኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት የሚከለከሉ ስርዓቶችን መጠበቅ
- ቢቻል ሚዜዎቹ ንስሀ አንዲገቡ ቤተክርስቲያን ታስተምራለች

2. ጊዜ ተክሊል

- ጧፍ እያበሩ ሌሊት 10 ሰዓት በቤተ መቅደስ ይገኛሉ
- ብሩህ ነጭ ልብስ ይለብሳሉ ይሄ የእግዚአብሔር ልጅ ሥለመሆናቸው የልጅነት ምሳሌ
- ጸሎተ ተክሊል ይፈጸማል
- ወንጌል ይሳለማሉ ቅዱስ ቃሉን የመጠበቃቸው ምሳሌ
- ቅባተ ሜሮን ይቀባሉ በዚሕም ይቀደሳሉ ፀጋን ያገኛሉ
- ቀለበት ያጠልቃሉ የኃይማኖት ምሳሌ
- አክሊል ይቀዳጃሉ የመንግስተ ሰማይ ምሳሌ
- አንድ መስቀል ያስጨብጧቸዋል የፈተና ምሳሌ
- ቅዱስ ቁርብን ይቀበላሉ ከሁለትነት ወደ አንድነት ይሸጋገራሉ፡፡

3. ድህረ ተክሊል፡

- በዝማሬ በደስታ በእልልታ በእምመናትፈት የጋብቻ ምስክር ወቀረት ይቀበላሉ
- ለዚህ ታላቅ ክብር ያበቃቸውን አምላካቸውን ያመሰግናሉ
- የጋብቻቸውን በዓል (ሰርግ) ያደርጋሉ
- ይመረቃሉ ስጦታ ይበረከትላቸዋል
- ሁለት ቀን ከሩካቤ ተጠብቀው ይቆያሉ
- ቅድስናቸውን ጠብቀው ትዳራቸውን (ኑሯቸውን) ይጀምራሉ

ባልና ሚስት ከሩካቤ ሚከለከሉባቸው ቀናት

- በእርግዝና ጊዜ ጽንሰዋ ከጎፋ ሆዲ ከሰፋ-ለህፃኑ ጤንነት
- በወሊድ (በእርስ) ጊዜ ከደዌ ስጋ ይጠበቃል
- በትክት (በወር አበባ) ጊዜ ከደዌ ስጋ ይጠበቃል
- በአብይት በዓላት - የነፍስን ፍቃድ ለመፈጸም
- በአጽዋማት - የነፍስን ፈቃድ ለመፈፀም

ጋብቻ የሚፀናው ደስታ የሚያስገኘው በምንድነው

ከጋብቻ በፊት

- ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ ይኸውም ለመልካም ነገር ተቃራኒ ከሆነ
- የኃይማኖት አንድነትና ጽናት
- የአላማ አድነትና ጽናት
- የዕድሜና የአስተሳሰብ መቀራረብ
- የጠባይ መጠናናት ደካማና ጠንካራ ጎኑን የሚወደውንና የሚጠላውን የወደፊት ዕቅዱና ወዘተ ..... ማወቅ
- መንፈሳዊ የአስተሳሰብ ብስለት
- ለመተዳደሪያ የሚሆን ገቢ መኖሪያ ገንዘብ አጠቃቀሙን፣ የማስተዳደር ችሎታው .... ማረጋገጥ

በጋብቻ ውስጥ

- በቅዱስ ቃሉ መመራት፡-በዚህውስጥ ትህትና፣ ትዕግስት፣ መተዛዘን፣ መደጋገፍ፣ መከባበር ወዘተ ....አለ መዝ 127፥1-4
- ለእኔ ብቻ አለማለት፡- በተለይ ልጆች ከተወለዱ በኋላ በንብረት በምግብ ወዘተ .... ሁሉም ነገር የጋራ መሆኑን ማወቅ እንኳን ቁሳቁስ ሰውነታቸውም የባልና ሚስቱ የጋራ ነው፡፡
- በአጠቃላይ እግዚአብሔር የሚከበርበትና የሚመሰገንበት ትንሹ ቤተክርስቲያን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ሰዎችም (ጎረቤቶችምን) በማህበረሰባዊ ሕይወት ማገልገል ይጠበቅበታል 1ጴጥ3፥1-6 "መልካም ስራን በመስራት ያጊጡ"

ቅዱስ ጋብቻና ፍቺ

ጋብቻ ቅዱስ ነው ፍቺ ግን ጉዳቱ አስከፊ በመሆኑ ከሚከተሉት ምክንያቶች በቀር አይፈቀድም

- ከሁለት አንዱ በሞት ሲለይ
- ከሁለት አንዱ በዝሙት ሲወድቅ ትክክለኛ ማስረጃ ከተገኘ ነው ቢሆንም በንስሐ መኖር ይችላል
- ከሁለቱ አንዱ የኃይማኖት ልዩነት ሲፈጠር

2.6 ምስጢረ ንስሐ

ትርጉም፡- ንስሐ፡- አዘነ፣ተፀፀተ፣ተቆጨ፣ክፉ አመሉን ተወ፣ጠባዩን ለወጠ ማለት ነው፡፡

- ኢሳ1፡18 ሕዝ18፡26፣ ሚል3፡7፣ሐዋ17፡30

ንስሐ፡- ሰው በፈፀመው ኃጢያት ተፀጽቶ ዳግም ላለመመለስ የሚወሰነው ውሳኔ ነው፡፡

ንስሐ፡- ከእግዚአብሔር የታዘዘ የኃጢያት መድኃኒት ነው

ስለምን ምስጢር ተባለ?

በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋ ስለሚገኝበት ነው፡፡

የሚታየው አገልግሎት፡- ካህኑ ሲናዘዝ ይፍታ ሲል

- ምዕመኑ ሲናዘዝ ቀኖናውን ሲፈፅም

- **የማይታየው አገልግሎት፡-** የኃጢያት ማሰሪያው ሲበጠስ

-

2.6.1 የንስሐ አጀማመር

ንስሐ ከኃጢያት መከሰት በኋላ በአዳምና በሔዋን ነው የተጀመረው፡፡ በበደሉት በደል ተጸጽተው ጉድጓድ ምሰው አመድ ነስንሰው ይቅርታ በጠየቁበት ጊዜ እግዚአብሔር ራራላቸው የድህነትን ተስፋ ስጣቸው በዕለተ ሐሙስ ወበ መንፈቅ ለሊት ይትወለድ እምወለተ ወለትከ "ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ፡፡ ሂኖ ክ24 እንዲል ያቺ በንስሐ ያገኛት ተስፋም እመቤታችን ነበረች፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሶሪያዊ በሰኞ ውዳሴ ማሪያም "ጌታ ልቡ ያዘነና የተከዘ አዳምን ነፃ ያወጣውና ወደቀደም ቦታው ይመልሰው ዘንድ ወደደ" ያለው ለዚህ ነው፡፡
ከአዳም መውደቅ በኋላ ኃጢያት በዓለም ነግስ ንስሐም ለኃጢያት መደምሰሻ የተሰጠ መድኃንት ነው (ሆነ)

2.6.2 የንስሐ ጥቅም

- ኤር8 ፥4-7 ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል/መታረቂያ መንገድ ነው/ እግዚአብሔር ይደሰትበታል ሉቃ15፥7-10

1. ኃጢያት ለማለት ማጣት ማለት ነው፡፡ ንስሐ ደግሞ እግዚአብሔርን ማግኘት ነው 2ቆሮ 5፥20
2. ስርየተ ኃጢያት ያሰጣል ሐዋ 3፥19 ሐዋ 2፥35

3. ፍፁም የሕሊና ሰላም ያስገኛል፡፡ ኃጢያት ሰላም ይነሳል 'ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል" ... ኢሳ 48፥22፣ ለጭንቀት ይዳረጋል ኤር፡13፥18 በተለይ ቅዱስ ቃሉን ለተማሩ
- በንስሐ የሚገኝ ሰላም፡- የህሊና ዕረፍት
- ሸክም ይቀላል
- ከዳኑበት ዘለቄታ ያለው ሰላም ነው፡፡
  "እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም" ዮሐ14፥27
- የዓለም ሰላም ጊዜያዊ ነው

የንስሐ አብነቶቻችን ከመጽሐፍት ቅዱስ

1. የነነዌ ሰዎች የንስሐ ሕይወትና ያገኙት ጥቅም ት.ዮና 1
2. የቅዱስ ዳዊትና የኦርዮን ታሪክ ትልቅ ማስተማሪያ ነው፡፡ ጊዜና 32፥24 ፡ 30፥10 ኢሳ 32፥1-6

3. የቅዱስ ጴጥሮስ የንስሐ ህይወቱና ኋላ ያገኘውን ክብር ማቴ 26፥69
4. የፊያታዊ ዘየማን እምነት (ታሪክ) ሉቃ23፤ንስሐ የሚገባ ሰው ከለመነው በላይ እንደሚያገኝ አብነት ነው፡፡
5. የዮሐንስ መጥምቅ ሰብኸት ማቴ 3፥1-6 ቤተክርስቲያናችንም በዝወትር ቅዳሴ "መንግስተ ሰማያት ቀርባላች ንስሐ ግቡ"በማለት ትገለገልበታለች አዋጅ ትነግርበታለች ወዘተ ...

2.6.3 የንስሐ ሂደትና አፈፃፀም

ቅድመ ንስሐ

1ኛ/ በሰሩት ኃጢያት በመፀፀትና የውሣኔ ሰው መሆን
2ኛ/ ቢቻል የሰሩትን ኃጢያት በማስታወሻ ጽፎ መያዝ
3ኛ/ ከመምህረ ንስሐ ጋር ቀጠሮ መያዝ

ጊዜ ንስሐ

1ኛ. መናዘዝ(ኑዛዜ ማድረግ) ሉቃ17፥14 "ሂድ ራስህን ለካህን አሳይ እንዲል በመምህረ ንስሐ ፊት አሞርና ግልጽ በሆነ

መንገድ እውነቱን መናዘዝ ምሳ 28፥13 ሐዋ 5፥1
2ኛ/ **ሲናዘዙ፡-** ምክንያት አለመደርደር ራስን ነፃ ለማድረግ መሞከር
3ኛ/ የካህኑን ምክርና ፈቃድ መፈፀም)ማክበር ይገባል፡፡ ብንገሰፅም እንኳን ልንቀበል ይገባል፡፡

2.6.4 ኑዛዜ ለማን?

ኑዛዜ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ስልጣን ባለው ካህን ፊት ነው የሚፈጸመው አንድ ሰው ኃጢአት ለመስራት ሲያስብ ሲሰራ እግዚአብሔር ያውቃል፤ያየዋል በቀጥታ መንገር እችላለሁ የሚል ቢኖር

- ለቀባሪ መርዶ መንገር ይቻላል
- ኃጢያት ለመስራት እግዚአብሔርን ያልፈራ ሰው ለመናዘዝ ጸጸት አያሳድርም በድጋሚ ኃጢአት ለመስራትም ይደፍራል
- ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰው ተደብቀው በሰሩት ክፉ ስራ ሳይፈሩ እርሱ ፊት ለመቆም ብቁ ነኝ የሚል ትዕቢት ያሳድራል
- እግዚአብሔር መርጦ ያከበራቸውን አለመቀበል ነው።

ሥለዚህ ቤተክርስቲያን የምታስተምረን ሥልጣኑ በተሰጣቸው ከህናት ፊት መናዘዝ ይገባል ካህኑ ፊት መናዘዝ በእግዚአብሔር ፊት መናዘዝ ማለት ነው ሐዋ 5፥1

ኑዛዜ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በአደባባይ በካህኑ ፊት ይፈጸም ነበር። ክርስቲያኖችም አገልጋዮችም እየበዙ ሲሄዱ ግን በየግል ሆኗል አፈፃፀሙም በካህኑ ፊት ለፊት ነው

ድህረ ንስሐ

ቀኖናውን ይቀበላል። ቀኖና የቅጣት ሥረዓት ማለት ነው አፈፃፀሙ ፡- የንስሐ አባቱ (የካህኑ) ልዩ መብት በመሆኑ ተነሳሒው አቅም ይወስናል። ቅጣቱም ጾም ፣ሥግደት፣ ምጽዋት ወዘተ ....ነው።

መድኃኒት ለአዋቂና ለሕፃናት እኩል እንደማይሰጥ የተነሳሒውን አቅም በማገናዘብ የሚሰጥ ሥረዓት ነው።

ቅጣቱን ሲፈጽም ካህኑ ኃጢያቱን እንዲሰረይ በጸሎት" በመጠየቅ" በድፍረት ሣናውቅ በስህተት

የሰራነውን ኃጢያት .... እግዚአብሔር ይፍታ" በማለት በተሰጣቸው የማሰርና የመፍታት ሥልጣን ከኃጢያት ይፈቱታል። ወደ ሥጋወደሙ በማቅረብም የሥጋና የነፍስ ድህነት እንዲያገኝ ያደርጋል።

2.6.5 ሥርዓተ ቁደር

ትርጉም፡- ቁደር ማለት የንስሃ ጥምቀት ማለት ነው

ስርዓተ ቁደር ለማን ይፈፀማል?

- ሃይማኖቱን ክዶ ለተመለሰ
- ካልተጠመቁ ጋር በዝሙት ለወደቀ
- መንኩሶ ላፈረሰ
- ጠንቋይ ቤት ለሄደ
- ሰው ለገደለ፣ወንበዴ ለሆነ፣ለሰረቀ(ሌባ)

2.6.8 ምዕመናን ከንስሐ የሚዘገዩበት ምክንያቶች

1ኛ/ **ከዕውቀት ማነስ** -- ሐዋ24፡25፡ሲራክ 7፡25፣መክ፡12፡1

- ገና ነኝ ኩፋ 4፡5 "እግዚአብሔር ቸር ነው እያልክ በኃጢያት ላይ ኃጢያት አትሰራ
- ዛሬ ነገ እያሉ ያሳለፉት የንስሐ እድል ነገ ላይ ላይገኝ ይችላል

2ኛ/ **ሥጋት** - ደግሜ ብበድልስ ምሳ 24፡16

ከንስሐ በኋላ ኑሮውን ገዳማዊ ሕይወት እንደመምራት በመቁጠር ሥጋት ውስጥ መግባት

ምስጥሬን ባይጠበቅስ በማለት

3ኛ/ ተስፋ መቁረጥ በደሌን ብዙ ነው ይቅርታ አላገኝም (ይቅር አይለኝም) ብሎ መደምደም 1ጴጥ 5፥6-8፣ ኢሳ1፥18

ተስፋ የቆረጠ ሰው ክርስቲያን አይደለም

የእኛ ተስፋ መቁረጥ ለጠላታችን ድል ነው ስለዚህ "ጠላቴ ሆይ ብወድቅ እነሳለሁና በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆነኛልና በእኔ ደስ አይበልህ" በማለት ወደ ህሊና መመለስ ያስፈልጋል ሚክ 7፥-8 ጸሎተ ቅዳሴ ላይ "በከመ ምህረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ" እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደበደላችን አይሁን እያልን የምንቀርበውም ለዚህ ነው። ዘማዊቷን ዩሐ 8 የህስቅያስንና የንስሐ አብነቶቻችን ላይ የጠቀስናቸውን ታሪክ ተመልከቱ።

2.6.9 የንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነትና፣ኃላፊነትና ድርሻ

1ኛ. የንስሐ አባት ኃላፊነት

ሀ/ መልካም እረኛ መሆን ዩሐ10፥1፣ ማቴ18፥21፣ ሕዝ 36፥ሚልክ 2፥7

ለ/ የንስሐ ልጆችን መከታተል ሐዋ15፥36፣ ኢሳ 28፥24፣ ሐጌ 2፥1

ክትትሉ በማስተማር ይኸውም የንስሐ ልጆቹን ቀን ወስኖ በመሰብሰብ አልያም በየቤታቸው በመሄድ (በተወሰነ ጊዜ) ማቴ 5፥16፣ ሉቃ11፥52

-በርህሀራሄ በመግለጽ በማበረታታት 1ሳሙ.1፥12፣ ኢዮ16፥4

የጠፉትን በመፈለግ

ሐ/ ስለ ልጆቹ መፀለይ ሐዋ 20፥31፣ ሉቃ13፥9፣ 1ጢሞ 2፥1-5

መ/ ሚስጥር ጠባቂ (ታማኝ) መሆን፡- ንስሐ የሚገባው ሰው መተማመን እንደሚያድርበት ያደርጋል።

2ኛ የንስሐ ልጅ ድርሻ

ሀ/ አባቱን ማክበር ሐዋ10፥16 1ጢሞ5 አካህናት ሆይ ሥቶማን ክብር ለክሙ ሶባ ትትካህኑ ምስለ እግዚኦት ሰማያት ምድርን የተሸማችሁ ካህናት ሆይ ከሰማይና ከምድር ጌታ ጋር ለማገልገል ትላካላችሁ ክብር ይገባችኋል። ቅዳሴ .አትናቴዎስ .ቁ96

ለ/ በሚያስፈልጋቸው መርዳት "ለሰራተኛ ደሞዝ ይገባዋል" እንዲል ማቴ10፥10 በገንዘብ ፣በጉልበት፣በእውቀትመርዳት ይገባልይኸውም እንደ አባት ነውና።

ሐ/ በግልጽ መቅረብ፡- ኑዛዜ ላይ የዘረዘረርነውን ተመልከት

መ/ በመልካም ምክሩ መጓዝ ፣ መታዘዝ ከእርሱ አለመራቅ መገናኘት

3ኛ. የአባትና የልጅ ግንኙነት እስከ ምን ድረስ ነው?

ሀ/ የቤተክርስቲያንን እምነት፣ስርዓትና ትውፊት የማይጥስ ከሆነ በየጊዜው ይቻላል

ለ/ እንቅፋት ከሚሆን የግንኙነት ጊዜን መቆጠብ

ሐ/ ጥቅምን ብቻ ያገናዘበ እንዳይሆን በመጠንቀቅ በተሰማሙበት የመገናኛ ቀን መጠያየቅ መረዳዳት ይችላሉ

አየንስሐ ባት መቀየር ይቻላል?

ከሚከተሉት ምክንያቶች በቀር አይቻልም

1. የነፍስ አባት በዕፍተ ስጋ ሲለዩ
2. የነፍስ አባት የኃይማኖት ሕፀፅ ሲገኝባቸው
3. በመኖሪያ ስፍራ ርቀት ለመገናኘት ፍጹም የማይቻል ከሆነ
4. ካህኑ ሲያሰናብቱ፡- ይኸውም በእርጅና፣የንስሐ ልጃቸውን ከኃጢያቱ አልመለስ ሲል ያሰናብታሉ

ቅጣት

ኃላፊነቱን በማይወጣ ኖላዊ (እረኛ) ካህንና ንስሐ በማይገባ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል

ለካህኑ፡- ሕዝ 34፥1-10 ቅጣት ምን እንደሆነ አስቀምጪል

ለምዕመኑ፡- ሉቃ 13 ፥1-6 "ንስሀ ባትገቡ እንገዲህ ትጠፋላችሁ" ይላል

2.7 ምስጢረ ቀንዲል

ትርጉም፡- ቀጥታ ትርጉሙ በዘይት የሚበራ መብራት ማለት ነው። በመጽሐፍት ቀንዲል ፀሎት ሲያደርግ የሚበራውን መብራት ይመለከታል

ቀንዲል፡- የሥጋና የነፋስ መድኃኒት ነው ይኸውም የነፍስ የኃጢያት ሥርዓት ከንስሐ ጋር ሲሆን ይገኝበታል ያዕ፥14 ?

ስለምን ምስጢር ተባለ?

የሕመምተኛው የነፍስ ቁስል በጸሎተ ቀንዲል እና በካህኑ ሱታፌ ሲደመስስ የሥጋውንና ቁስል ሲፈወስ በአይን ስለማይታይ ነው።

ይህ ቅዱስ ዘይት "ቅብዓ ቅዱስ" እየተባለ በምዕመናን ዘንድ ሲጠራ በስፋት ይታወቃል

አመሰራረት

ለህሙማን የሚረዳው ይህ ቅብዓ ቅዱስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀደማዛሙርቱ በአጋንንትና በደዌያት ላይ ስልጣኑን በሰጣቸዉ ጊዜ ነው ማቴ10፥8፣ ማቴ18፥18" .. ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየተቀቡ ፈወሳቸው...." ማር 6፥7 እንዲል

አዘገጃጀት

ቀንዲል የሚዘጋጀው ከወይራ ዘይት ሲሆን ፈውስ (ዘይት) የሚሆነው በጸሎት ነው።

3ኛ. የአባትና የልጅ ግንኙነት እስከ ምን ድረስ ነው?

ሀ/ የቤተክርስቲያንን እምነት፣ስርዓትና ትውፊት የማይጥስ ከሆነ በየጊዜው ይቻላል

ለ/ እንቅፋት ከሚሆን የግንኙነት ጊዜን መቆጠብ

ሐ/ ጥቅምን ብቻ ያገናዘበ እንዳይሆን በመጠንቀቅ በተሰማሙበት የመገናኛ ቀን መጠያየቅ መረዳዳት ይችላሉ

የንስሐ ባት መቀየር ይቻላል?

ከሚከተሉት ምክንያቶች በቀር አይቻልም

1. የነፍስ አባት በዕፍተ ስጋ ሲለዩ
2. የነፍስ አባት የኃይማኖት ሕፀፅ ሲገኝባቸው
3. በመኖሪያ ስፍራ ርቀት ለመገናኘት ፍጹም የማይቻል ከሆነ
4. ካህኑ ሲያሰናብቱ፡- ይኸውም በእርጅና፣የንስሐ ልጃቸውን ከኃጢያቱ አልመለስ ሲል ያሰናብታሉ ቅጣት

- ኃላፊነቱን በማይወጣ ኖላዊ (እረኛ) ካህንና ንስሐ በማይገባ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል

ለካህኑ፡- ሕዝ 34፥1-10 ቅጣት ምን እንደሆነ አስቀምጪል

ለምዕመኑ፡- ሉቃ 13 ፥1-6 "ንስሀ ባትገቡ እንገዲህ ትጠፋላችሁ" ይላል

2.7 ምስጢረ ቀንዲል

ትርጉም፡- ቀጥታ ትርጉሙ በዘይት የሚበራ መብራት ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍት ቀንዲል ፀሎት ሲያደርግ የሚበራውን መብራት ይመለከታል

ቀንዲል፡- የሥጋና የነፋስ መድኃኒት ነው ይኸውም የነፍስ የኃጢያት ሥርዓት ከንስሐ ጋር ሲሆን ይገኝበታል ያዕ፥14 ?

ስለምን ምስጢር ተባለ?

የሕመምተኛው የነፍስ ቁስል በጸሎተ ቀንዲል እና በካህኑ ሱታፌ ሲደመሰስ የሥጋውንና ቁስል ሲፈወስ በአይን ስለማይታይ ነው፡፡

- ይህ ቅዱስ ዘይት "ቅብዓ ቅዱስ" እየተባለ በምዕመናን ዘንድ ሲጠራ በስፋት ይታወቃል

አመሰራረት

ለህሙማን የሚረዳው ይህ ቅብዓ ቅዱስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀደማዛሙርቱ በአጋንንትና በደዌያት ላይ ስልጣኑን በሰጣቸዉ ጊዜ ነው ማቴ10፥8፣ ማቴ18፥18" .. ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየተቀቡ ፈወሳቸው...." ማር 6፥7 እንዲል

አዘገጃጀት

ቀንዲል የሚዘጋጀው ከወይራ ዘይት ሲሆን ፈውስ (ዘይት) የሚሆነው በጽሎት ነው፡፡

ከጠበል ጋር ተቀላቅሎ ቢጠጣ ችግር አለውን?
ቀንዲል ይቀባል እንጂ አይጠጣም

2.7.1 አፈፃፀም

- ቀንዲል የሚፈፀመው ለሕመምተኛ ሲሆን በቁስና ክቅስና በላይ ማዕረግ ባለው የኃይማኖት አባት ይፈጸማል፡፡ "ከእናንተ መካከል የታመመ ቢኖር የቤተክርስቲያን ቀሳውስት (ሽማግሌዎች) ይጠራ በቴስልሉ ላይም ዘይት ቀብተው ይጸልዩበት ይድናል.... ኃጢያትም ሰርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል"ያዕ5፡ ባጠቃላይ ነንስሐ አባት ይፈጸማል፡፡
- ንስሐ አባት በድውዩ ላይ የሚጸልዩለት ቀንዲል ይሆናል፡፡
- ከታማሚው ሆነ ከቤተሰብ እምነትና የንስሐ ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡
- ሕመምተኛው እምነት ኖሮት ንስሐ ገብቶ በጠበልም በቀንዲልም ፈውስ ካላገኘ ተስፋ መድረጥ አይገባም ይልቁንስ ፡--

1ኛ/ ደጋግሞ ምስጢር መፈፀም
2ኛ/ እግዚአብሔር ለእርሱ ህይወት በጎ ዓላማ እንዳለው አምኖ መቀበል፡፡
3ኛ/ ተስፋ መቁርጥ ክርስትናን መተው (መካድ) እንደሆነ ማወቅ ይጠበቅበታል
4ኛ/ ንስሐ ገብቶ ቀንዲል ስርዓትን ፈጽሞ ሞት እንኳ ቢመጣ ኃጢያቱን ስለተሰረየ ገነት (መንግስተ ሰማያት) እንደሚገባ እግዚአብሔር ቃሉን እንደማያጥፍ እርሱም ቤተሰቡም ማመን አለባቸው

- የነፍሱን ኃጢያት በስጋ ላይ በሽታን ወይም ሌላ መከራን በማምጣት እግዚአብሔርን ልጆቹን ሊቀጣን ሊገስጸን እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ "አባቱ የማየቀጣው ልጅ ዲቃላ ነውና" እግዚአብሔር የሚወደውን ይገስጻል" እንዲል "በሥጋ መከራ የተቀበለ ኃጢያትን ትቶአል" 1ጴጥ 4፥2 ስለዚህ የሥጋ ሕመም እያስጨነቀን ሥለ ነፍስ ድህነት የመጣ ነውና

ስለዚህ ቅንዲል ከንስሐ ጋር ከሆነ ከነፍስ ሞት ያድናል፣የመንፈስ እርካታን የውስጥ ሰላምን ይሰጣል

የምዕመናን ድርሻ

1. የወይራ ዘይቱን ገዝቶ ለንስሐ አባት መስጠት
2. ሥለ አቀማመጡና አፈፃፀሙ በካህኑ ምክር መመራት
3. ዘይቱ ቅብአ ቅዱስ ከሆነ እንደማይሸጥ ማወቅ ማሳወቅ

የካህኑ ድርሻ

1.ሚስጥሩን በአግባቡ መፈፀም፡፡ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በሚያዘው መሰረት ለምዕመናን ማስተማር
2. ሕመምተኛውን መንከባከብ፣ማጽናናት ማበረታታት እና ትህትና በተመላበት አንደበት ፍቅርንና ርህራሄን ማሳየት
3. ቀንዲል ከሚደገሙ ሚስጥራት አንዱ ነው፡፡

ወስብሀት ለእግዚአብሔር!